የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

| | | |
|---|---|---|
| አሥራስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፭<br>አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፰ ቀን ፪ሺ፪ | በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ<br>የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 16th Year No. 45<br>ADDIS ABABA 4th Augest, 2010 |


ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፮፻፸፰/፪ሺ፪ ዓ.ም

የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ...... ገጽ ፭ሺ፫፻፹፭


**CONTENTS**


Proclamation No. 678/2010

Mining Operations Proclamation …Page 5385


### አዋጅ ቁጥር ፮፻፸፰/፪ሺ፪

### ዘላቂ የሆነ የማዕድን ሃብት ልማት ለማምጣት የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት የመንግሥትና የሕዝብ መሆኑ የተደነገገ በመሆኑና መንግሥትም ይህን ሀብት የመጠበቅ ኃላፊነት የተጣለበት በመሆኑ፤

ማዕድናት የማይታደሱ የተፈጥሮ ሃብቶች በመሆናቸው ጥበቃቸውና ለመላ ኢትዮጵያዊያን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጥቅም መዋላቸው በመንግሥት መረጋገጥ ያለበት ስለሆነ፤

ለአሁኑና ለወደፊቱም ትውልድ ጥቅም አካባቢን መጠበቅና ከሥነምህዳር ጋር የሚጣጣም ዘላቂነት ያለው የማዕድን ልማትን ማረጋገጥ የመንግሥት ኃላፊነት በመሆኑ፤

እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የማዕድን ሥራዎችን በተመለከተ አዲስ ሕግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### PROCLAMATION NO. 678/2010.

### A PROCLAMATION TO PROMOTE SUSTAINABLE DEVELOPMENT OF MINERAL RESOURCES

WHEREAS the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia provides that the right to ownership of all natural resources of Ethiopia is exclusively vested in the government and in the peoples' of Ethiopia and that the government is the custodian thereof;

WHEREAS minerals are non-renewable natural resources and that the government shall ensure the conservation and development of these resources to the socio-economic progress of all Ethiopians;

WHEREAS it is the obligation of the government to protect the environment for the benefit of present and future generations and to ensure ecologically sustainable development of minerals;

WHEREAS to achieve these ends it is essential to promulgate a new law on mining operations;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 12.50

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር ፮፻፸፰/፪ሺ፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩/ "መመሳጠር የሌለበት ግብይት" ማለት የሚሸጠውን የማዕድን ሃብት ጥራትና መጠን ብቻ ግምት ውስጥ በማስገባት ምንም ሽርክና ወይም የተለየ ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በግልጽ ገበያ ላይ በነፃ ድርድር የዚህ አይነት ሃብት በተመሳሳይ በሚሸጥበት ሁኔታ ላይ ተመስርቶ የሚኖረው የገበያ ዋጋ ነው፤

፪/ "ባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ" ማለት አብዛኛው ተግባር በእጅ የሚከናወን እና ተቀጣሪ ሰራተኛ የማይሳተፍበት በግለሰቦች ወይም በኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚከናወን የማዕድን ማምረት ሥራ ነው፤

፫/ "የኮንስትራክሽን ማዕድን" ማለት ማናቸ-ውም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለኮንስትራክሽን በግብዓትነት የሚያገለግል እንደ ዕብነበረድ፣ ግራናይት፣ ላይምስቶን ባዛልት፣ አሸዋ፣ ጠጠር፣ ኢግኒምብራይ-ትና የሸክላ አፈር የመሰለ ማዕድን ሲሆን፣ ሚኒስቴሩ በመመሪያ የኮንስትራክሽን ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ብረት ነክ ያልሆነ ሌላ ማዕድንን ይጨምራል፤

፬/ "አላቂ ዕቃዎች" ማለት ለማዕድን ሥራ የሚያስፈልጉና በማዕድን ሥራው ወቅት በጥቅም ላይ ውለው የሚተኩ ኬሚካ-ሎችን ጨምሮ ሚኒስቴሩ በመመሪያ አላቂ ዕቃዎች ብሎ የሚሰይማቸው ናቸው፤

፭/ "ቀን" ማለት በቀን መቁጠሪያ ላይ የሰፈረ ማንኛውም ቀን ሲሆን፣ በዚህ አዋጅ፣ በደንብ ወይም በመመሪያ የተመለከተ ተግባርን ለማከናወን የተወሰኑ ቀናት ተቆርጠው ከሆነ ቀናቱ የሚወሰኑት የመጀመሪያውን ቀን በመቀነስ እና እሁድና ቅዳሜ ወ [illegible] በሕዝብ በአላት ላይ እስካልዋለ ድረስ የመጨረሻውን ቀን በመጨመር ይሆናል፤

## PART ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Mining Operations Proclamation No. 678/2010".

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "arms length transaction" means the value of any mineral resource at a commercial price that would have been agreed to by unconnected persons for such a resource if those persons were freely negotiating on the open market under similar circumstances taking into account solely the characteristics of quality and quantity of the mineral resource transferred;

2/ "artisanal mining" means a mining operation carried out by individuals or cooperatives which is mostly of manual nature and that does not involve the engagement of employed workers;

3/ "construction mineral" means any mineral directly or indirectly used as input for construction purposes such as marble, granite, limestone, basalt, sand, aggregate, ignimbrite and clay and includes any other non-metallic mineral designated as such by directives of the Ministry;

4/ "consumables" means anything needed for mining operations that are expendable and replaced during service including chemicals and those the Ministry may, by directives, designate as consumables;

5/ "day" means a calendar day and when any particular number of days are prescribed for the doing of any thing in this Proclamation, regulations or directives, those days shall be determined by excluding the first and including the last day, unless the last day falls on a Saturday, a Sunday or any public holiday;

፮/ "መመሪያ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣ መመሪያ ነው፤

፯/ "የአገር ውስጥ ባለሀብት" ማለት የኢንቨስትመንት ካፒታል በሥራ ላይ ያዋለ ኢትዮጵያዊ ወይም መደበኛ መኖሪያው ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ሲሆን፣ መንግስትንና የመንግስት የልማት ድርጅትን እንዲሁም እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ አገር ዜጋን ይጨምራል፤

፰/ "ምርመራ" ማለት ሆን ብሎ ማዕድን ለማግኘት በማናቸውም የገፀምድር ወይም ከርሰ ምድር፣ በውሃ አካላት እንዲሁም ቀደም ሲል ተቆፍሮ በወጣና በቀረ የተቆለለ ማዕድን አዘል አፈር ወይም አለት ውስጥ በአካባቢ ላይ ለውጥ በሚያስከትል መልኩ በፎቶግራፍና ምስሎች፣ በጂኦሎጂ፣ በጂኦፊዚክስ፣ በጂኦኬሚስትሪ፣ በተለያዩ የጉድጓድ ቁፋሮና በመሳሰሉት ዘዴዎች አማካኝነት የማዕድኑን መኖር፣ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውን እና መጠኑን ለማወቅና ለማጣራት የሚደረግ ሥራ ነው፤

፱/ "የውጭ ባለሀብት" ማለት የውጭ ካፒታል ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ኢንቨስት ያደረገ የውጭ ዜጋ ወይም በውጭ ዜጎች ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት ሲሆን እንደ ውጭ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ በውጭ አገር የሆነ ኢትዮጵያዊን ይጨምራል፤

፲/ "መንግሥት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ማለት ሲሆን እንደአግባቡ ክልሎችንም ይጨምራል፤

፲፩/ "የኢንዱስትሪ ማዕድን" ማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለኢንዱስትሪ በግብዓትነት የሚያገለግል እንደ ካኦሊን፣ ቤንቶናይት፣ ኳርትዝ፣ የድንጋይ ከሰል፣ ላይምስቶን፣ ጂፕሰም፣ ፑሚስ፣ የሸክላ አፈርና ግራፋይት የመሰለ ማንኛውም ማዕድን ሲሆን፣ ብረት ነክና የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ሳይጨምር ሚኒስቴሩ በመመሪያ የኢንዱስትሪ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማንኛውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤

፲፪/ "ከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ" ማለት የከበሩ ወይም በከፊል የከበሩ ድንጋዮችን የማምረት ሥራን በሚመለከት ካልሆነ በቀር ከማዕድኑ ሥፍራ በዓመት የሚነሳው ማዕድን አዘል አፈርና ድንጋይ መጠን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፴፭) ከተመለከተው መጠን በላይ የሆነ ማዕድናትን የማምረት ሥራ ነው፤

6/ "directives" means directives issued pursuant to this Proclamation;

7/ "domestic investor" means an Ethiopian or a foreign national permanently residing in Ethiopia having made an investment, and includes the government, public enterprises as well as a foreign national of Ethiopian origin and desiring to be considered as a domestic investor;

8/ "exploration" means searching for any mineral by means of photographs, images, geological, geochemical, geophysical and drilling methods which disturbs the surface or subsurface of the earth, including any portion of the earth that is under water, or in or on any residue stockpile or residue deposit, in order to establish the existence of any mineral and to determine the extent and economic value;

9/ "foreign investor" means a foreign national or an enterprise owned by foreign nationals, having invested foreign capital in Ethiopia, and includes an Ethiopian permanently residing abroad preferring treatment as a foreign investor;

10/ "government" means the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes states where appropriate;

11/ "industrial mineral" means any mineral directly or indirectly used as industrial input such as kaolin, bentonite, quartz, coal, limestone, gypsum, pumice, clay and graphite and includes any other mineral the Ministry may, by directives, designate as such, excluding metallic and precious and semi-precious minerals;

12/ "large scale mining" means any mining operation of which the annual run-of-mine ore exceeds the limit stated in sub-article (35) of this Article with the exception of precious and semi-precious stones;

፲፫/ "ፈቃድ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ የማዕድን ቅኝት፣ ምርመራ፣ ይዞ መቆየት ወይም ማምረት ፈቃድ ነው፤

፲፬/ "የፈቃድ ክልል" ማለት ማናቸውም ፈቃድ የተሰጠበት ሥፍራ ነው፤

፲፭/ "ባለፈቃድ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የቅኝት ፈቃድ፣ የምርመራ ፈቃድ፣ ይዞ የመቆየት ፈቃድ ወይም የማምረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ተተኪው ነው፤

፲፮/ "ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን" ማለት እንደ አግባቡ የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ወይም ማዕድን ዘርፍን በሚመለከት ኃላፊነት የተሰጠው የክልል አካል ነው፤

፲፯/ "ብረት ነክ ማዕድን" ማለት እንደ ብረት፣ መዳብ፣ ነሐስ፣ እርሳስ፣ ክሮማይት፣ ኒኬል፣ ታንታለም ማንጋኒስ የመሰለ ማዕድን ሲሆን፣ የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን ሳይጨምር ሚኒስቴሩ በመመሪያ ብረት ነክ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማንኛውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤

፲፰/ "ማዕድን ማምረት" ማለት በማናቸውም አይነት ዘዴ በሚከናወን ሥራ ማዕድንን በገፀ ምድር፣ በከርሰ ምድር ወይም በውሃ አካላት ከሚገኝ የማዕድን ክምችት ወይም ተራፊ የማዕድን ክምችት ውስጥ ለማውጣት የሚደረግ ሥራ ሲሆን ከዚህ ጋር የተያያዘ ማከማቸትን፣ ማዘጋጀትን፣ ፕሮሰስ ማድረግን (ማቅለጥንና ማጣራትን ሳይጨምር)፣ ማጓጓዝንና መሸጥን ይጨምራል፤

፲፱/ "ማዕድን" ማለት ማናቸውም ዋጋ ያለው በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ በተፈጥሮ በመሬት ላይ ወይም ውስጥ፣ በውሃ ውስጥ ወይም ስር የሚገኝ በጂኦሎጂ ሂደት ወይም ሁኔታዎች የተፈጠረ ሲሆን ቀደም ሲል ተቆፍሮ በወጣና ተራፊ የተቆለለ ማዕድን አዘል አፈር ወይም በቀሪ የማዕድን ክምችት ውስጥ የሚገኝ ማዕድንን ይጨምራል፤ ሆኖም የሚከተሉትን አይጨምርም፡-

ሀ) ከውስጡ ማዕድን ለማውጣት ከሚውል እንደ ብራይን ውሃ በስተቀር ሌላ ውሃን፤

13/ "license" means a reconnaissance license, an exploration license, a retention license or a mining license issued pursuant to this Proclamation;

14/ "license area" means any area which is the subject of a license;

15/ "licensee" means the holder of a reconnaissance license, an exploration license, a retention license or a mining license or any successor thereof;

16/ "licensing authority" means the Ministry of Mines and Energy or a state organ in charge of the mining sector as appropriate;

17/ "metallic mineral" means any mineral such as iron, copper, zinc, lead, chromites, nickel, tantalum and manganese and includes any other mineral the Ministry may, by directives, designate as such excluding precious and semi-precious minerals;

18/ "mining" means any operation or activity directed at extracting minerals from a mineral deposit on or in the earth and water, any residue deposit or residue stockpile by any method, and any operation incidental thereto, such as storage, treatment, processing (excluding smelting and refining), transportation and disposal;

19/ "mineral" means any mineral substance of economic value, whether in solid, liquid or gaseous form, occurring naturally on or within the earth or in or under water and which was formed by or subjected to a geological process, and includes any mineral occurring in residue stockpiles or in residue deposits, but excludes:

a) water, other than water used for the extraction of any mineral such as brine;

ለ) አግባብ ባለው የነዳጅ ሕግ ትርጓሜ የሚካተቱ የተፈጥሮ ዘይትና ጋዝን፤

ሐ) ለም አፈርን (ላይኛው አፈር) እና ነዳጅ አዘል አለትን (ነዳጅ አዘል ሼል)፤

፳/ "የማምረት ፈቃድ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ የከፍተኛ ደረጃ፣ የአነስተኛ ደረጃ ወይም የባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ነው፤

፳፩/ "የማዕድን ሥራ" ማለት ከማዕድን ቅኝት፣ ምርመራ፣ ይዞ መቆየት ወይም ማምረት ጋር የተያያዘ ተግባር ነው፤

፳፪/ "የማዕድን መብት" ማለት ከቅኝት፣ ከምርመራ፣ ይዞ ከመቆየትና ከማምረት ፈቃድ ጋር የተያያዘ መብት ነው፤

፳፫/ "ሚኒስቴር" ማለት የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር ወይም ተተኪው ነው፤

፳፬/ "የከበረ ማዕድን" ማለት እንደ ኘላቲነየም፣ ወርቅና ብር የመሰለ የከበረ ብረት ነክ ማዕድን ወይም እንደ አልማዝ፣ ሩቢ፣ ኢመራልድና ሳፋየር ያለ የከበረ ድንጋይ ሲሆን፣ ሚኒስቴሩ በመመሪያ የከበረ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማናቸውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤

፳፭/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፮/ "ፕሮሰስ ማድረግ" ማለት ማዕድንን በቱለያየ ዘዴ ማውጣት፣ መቆፈር፣ ማጥለል፣ ማድረቅ፣ በዓይነት መመደብ፣ መፍጨት፣ ማበጠር፣ ማጠብ፣ ማድቀቅ ወይም ወደጋዝ መለወጥ ነው፤

፳፯/ "ቅኝት" ማለት ማናቸውንም ማዕድን ለማግኘት የሚካሄድ አጠቃላይ የሆነ የማዕድን ፍለጋ ሥራ ነው፤

፳፰/ "መዝገብ" ማለት በዚህ አዋጅ የተመለከ-ተው የማዕድን መብቶች የተመዘገቡበት መዝገብ ወይም የኤሌክትሮኒክስ የማዕድን ካዳስተር ነው፤

፳፱/ "ደንብ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣ ደንብ ነው፤

b) natural gas and petroleum as defined in the relevant petroleum

c) top soil and oil shale;

20/ "mining license" means large scale, small scale or artisanal mining license issued pursuant to this Proclamation;

21/ "mining operation" means any activity associated with or connected to reconnaissance, exploration, retention or mining;

22/ "mineral right" means any right associated with reconnaissance license, exploration license, retention license or mining license;

23/ "Ministry" means the Ministry of Mines and Energy or any successor thereof;

24/ "precious mineral" means precious metallic mineral such as platinum, gold and silver or precious stone such as diamond, ruby, emerald and sapphire and includes any other mineral the Ministry may, by directives, designate as such;

25/ "person" means any natural or juridical person;

26/ "processing" means winning, extracting, concentrating, calcining, classifying, crushing, screening, washing, reduction, or gasification of a mineral;

27/ "reconnaissance" means any operations carried on in a general search for any mineral;

28/ "register" means the register of mining rights or the electronic mining cadastre provided for in this Proclamation;

29/ "regulation" means regulation issued pursuant to this Proclamation;

፴/ "ተራፊ ክምችት" ማለት የማዕድን ፈቃድ ሲቋረጥ፣ ሲሰረዝ ወይም ዘመኑ ሲያበቃ የነበረ ማናቸውም ተራፊ ማዕድን አዘል ቁልል ነው፤

፴፩/ "ተራፊ ማዕድን አዘል ቁልል" ማለት ከማዕድን ሥራ የተገኘ ወይም በማዕድን ሥራው ምክንያት የወጣና በማዕድን ባለፈቃዱ እንደገና ጥቅም ላይ ለማዋል ታስቦ ተቆልሎ፣ ተቀምጦ ወይም ተጠራቅሞ የነበረ ወይም የተተወ ማናቸውም ፍራሽ፣ ውዳቂ፣ አሰር፣ ዝቃጭ፣ ብጣሪ፣ ቆሻሻ አዘል ድፍርስ፣ ውዳቂ ድንጋይ፣ ከብረት ማቅለጫ የሚወጣ አሸዋ፣ የማበልጸጊያ ፋብሪካ ቆሻሻ፣ አመድ ወይም ማናቸውም ተረፈ ምርት ነው፤

፴፪/ "ሮያሊቲ" ማለት የማዕድን ሀብት ባለቤት ለሆነው መንግሥትና ሕዝብ ባለፈቃድ ከማዕድን ማመረቻ ቦታ ላይ ከሚያመርተው የማዕድን /ናት/ምርት በየጊዜው በመቶኛ እየተሰላ የማምረቻና ሪስክ ወጪን ሳይጨምር የሚከፍለው ክፊያ ነው፤

፴፫/ "የሽያጭ ዋጋ" ማለት ከኢትዮጵያ ወደውጭ ሀገር በሚላክበት ኬላ (ፎብ) ወይም ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ሲሆን አቅርቦቱ የተፈፀመበት ቦታ የማዕድኑ የገበያ ዋጋ የሚከተለው ተቀንሶለት ነው፡-

ሀ) ማዕድኑን ከተመረተበት ቦታ ወደ ውጭ ሀገር እስከሚላክበት ኬላ ወይም ማስረከቢያ ቦታ ድረስ የኢንሹራንስና ከማጓጓዝ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ወጪዎች ተጨምረው የወጣው የትራንስፖርት ዋጋ፤እና

ለ) የማበልጸጊያ ወጪዎቹ እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ በማዕድኑ ሥፍራ በመደበኛነት ከሚደረጉ ሂደቶች ጋር የተያያዙ ካልሆነ በቀር ማዕድኑን ለማቅለጥና ለማጣራት የወጡ ወይም ሌሎች የማበልጸጊያ ወጪዎች፤

፴፬/ "በከፊል የከበረ ማዕድን" ማለት ለማስዋቢያነት የሚውል ወጥ ወይም በተፈጥሮአዊ አንድነት የተጣመረ እንደ ኦፓል፣ ሮዶላይት፣ ኦሊቪን፣ ጃዲይትና ላዙራይት የመሰለ ማዕድን ሲሆን፣ የከበሩ ማዕድናትን ሳይጨምር ሚኒስቴሩ በመመሪያ በከፊል የከበረ ማዕድን ብሎ የሚሰይመውን ማንኛውንም ሌላ ማዕድን ይጨምራል፤

፴፭/ "አነስተኛ የማዕድን ማምረት ሥራ» ማለት ከማዕድኑ ሥፍራ በአመት የሚመረተው የማዕድን አዘል አፈርና ድንጋይ መጠኑ ከሚከተለው የማይበልጥ ማዕድን የማምረት ሥራ ነው፡-

30/ "residue deposit" means any residue stockpile remaining at the termination, revocation or expiry of any mining license;

31/ "residue stockpile" means any debris, discard, tailings, slimes, screening, slurry, waste rock, foundry sand, beneficiation plant waste, ash or any other product derived from or incidental to a mining operation and which is stockpiled, stored or accumulated for potential re-use, or which is disposed of, by the holder of a mining license;

32/ "royalty" means the payment to the government and peoples' who are the sole owners of the mineral resources to be made by the licensee for producing minerals from the production site of minerals and the percentage rate of such payment is to be assessed from time to time excluding the price of production and risk expenditures;

33/ "sales price" means the commercial price of minerals at the point of export from Ethiopia (FOB) or, in the case of consumption within Ethiopia, at the point of delivery within Ethiopia, less:

a) the cost of transportation, including insurance and handling charges, from the mining area to the point of export or delivery; and

b) the cost of smelting and refining or other processing costs unless such other processing costs relate to processing normally carried out in Ethiopia in the mining area;

34/ "semi-precious mineral" means gem stones that are used for jewellery such as opal, rhodolite, olivine, jadite and lazurite and includes any other mineral the Ministry may, by directives, designate as such, excluding precious minerals;

35/ "small scale mining" means any mining operation of which the annual run-off mine ore does not exceed:

ሀ) ወርቅ፣ ፕላቲኒየም፣ ብርና ሌሎች የከበሩና በከፊል የከበሩ ማዕድናትን በሚመለከት:-

(፩) በደለል ላይ ለሚካሄዱ ሥራዎች ፩፻ሺ ሜትር ኩብ፤

(፪) በጽንስ ማዕድን ክምችቶች ላይ የሚካሄዱ ሥራዎች ፸፭ሺ ቶን፤

ለ) እንደ ብረት፣ እርሳስ፣ መዳብና ኒኬል የመሳሰሉ ሜታል ማዕድናትን በሚመለከት:-

(፩) በመሬት ላይ ለሚካሄዱ ሥራዎች ፩፻፶ሺ ቶን፤

(፪) በመሬት ውስጥ ለሚካሄዱ ሥራዎች ፸፭ሺ ቶን፤

ሐ) እንደ ካኦሊን፣ ቤንቶናይት፣ ዲያቶማይት፣ ዶሎማይት ኳርትዝና የድንጋይ ከሰል የመሳሰሉ የኢንዱስትሪ ማዕድናትን በሚመለከት ፩፻፳ሺ ቶን፤

መ) የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በሚመለከት:-

(፩) አሸዋ፣ ጠጠር፣ ፑሚስ፣ ኢግኒምብራይት፣ የሸክላ አፈርና የመሳሰሉትን በሚመለከት ፹ሺ ሜትር ኩብ፤

(፪) እብነበረድ፣ ግራናይትና የመሳሰሉትን የዳይሜንሽን ድንጋዮች በሚመለከት ፲ሺ ሜትር ኩብ፤

ሠ) የጂኦተርማል ክምችትን በሚመለከት:-

(፩) ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛና ለሕክምና አገልግሎት የሚውሉትን በሚመለከት ፪ሚሊዮን ሜትር ኩብ፤

(፪) ለኢንዱስትሪና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውሉትን በሚመለከት ፳፭ ሜጋዋት ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ኃይል ሊሰጥ የሚችል የጂኦተርማል እንፋሎት፤

ረ) ከድንጋይ ወይም ከብራይን የሚመረቱ የጨው ዓይነቶችን በሚመለከት ፲፬ሺ ቶን፤

፴፮/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን፣ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

a) regarding gold, platinum, silver and other precious and semiprecious minerals:

(1) 100,000m$^3$ for placer operation;

(2) 75,000 tons for primary deposit mining;

b) regarding metallic minerals such as iron, lead, copper and nickel:

(1) 150,000 tons for open pit mining;

(2) 75,000 tons for under ground mining operation;

c) 120,000 tones for industrial minerals such as kaolin, bentonite, diatomite, dolomite, quartz and coal;

d) regarding construction minerals:

(1) 80,000 m$^3$ for sand, gravel, pumice, ignimbrite, clay and the like;

(2) 10,000m$^3$ for dimension stones such as marble and granite;

e) regarding geothermal deposit:

(1) 2,000,000m$^3$ for bathing, recreational and medicinal purpose;

(2) 25 mega watt or geothermal steam capable of generating equivalent power for industrial and other purposes;

f) 14,000 tons for salts extracted from brines;

36/ "state" means any state specified under Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

፴፯/ "ስትራቴጂክ ማዕድን" ማለት ሚኒስቴሩ በመመሪያ ስትራቴጂክ ማዕድን ብሎ የሚሰይመው ማንኛውም ማዕድን ነው፤

፴፰/ "ማስተላለፍ" ማለት መሸጥ፣ በእዳ ማስያዝ፣ ማውረስ፣ መዳረግ ወይም በሌላ መንገድ ማስተላለፍ ነው፤

፴፱/ "የሥራ ፕሮግራም" ማለት እንደነገሩ አግባብነት ለምርመራ ወይም ለማምረት ሥራ የሚቀርብ ዝርዝር ስራውን፣ ሥራው የሚከናወንበትን ጊዜ፣ ወጪውን፣ መዋቅሩንና የሰው ኃይል ስብጥሩን የሚያመለክት ዕቅድ ነው፤

፵/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል።

## ፫. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ግዛት ውስጥ በሚካሄዱ የማዕድን ሥራዎችና ተዛማጅ ተግባራት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## መሰረታዊ መርሆዎችና ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## ፬. ዓላማ

የዚህ አዋጅ አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ መንግሥት የሀገሪቱን የማዕድን ሃብት ስለመጠበቅ የተጣለበትን ኃላፊነት ተግባራዊ ማድረግ፤

፪/ የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማት ማስፋፋት፤

፫/ የኢትዮጵያዊያንን የሥራ እድል ማስፋፋትና ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማሳደግ፤

፬/ በማዕድን ምርመራና ማምረት ሥራ የተሰማሩትን ባለሀብቶች የይዞታ ዋስትና ማረጋገጥ፤ እና

፭/ የሀገሪቱ የማዕድን ሀብት ሥርዓትንና ዘላቂነት ባለው ሁኔታ መልማቱን ማረጋገጥ።

37/ "strategic mineral" means any mineral the Ministry may, by directives, designate as such;

38/ "transfer" means a sale, encumbrance, inheritance, assignment or any other transfer;

39/ "work program" means the program of work for exploration or mining, as the case may be, that shows details of the work, the time schedule, the required budget, the organizational structure and its manning;

40/ a expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Scope of Application

This Proclamation shall apply to and govern the conduct of all mining operations and related activities within the territory of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

## PART TWO

## FUNDAMENTAL PRINCIPLES AND GENERAL PROVISIONS

## 4. Objectives

The objectives of this Proclamation are to:

1/ give effect to the principle of the custodianship of the country's mineral resources by the government;

2/ promote socio-economic growth of the country;

3/ promote employment and advance the social and economic welfare of all Ethiopians;

4/ provide for security of tenure for all investors in respect of exploration and mining operations; and

5/ ensure that the country's mineral resources are developed in an orderly and sustainable manner.

## ፭. ስለማዕድን ሃብት ጠባቂነት

፩/ በኢትዮጵያ ወሰን ውስጥ በገጸ ምድርም ሆነ በከርሰ ምድር በተፈጥሮአዊ ሁኔታው የሚገኝ የማዕድን ሀብት የመንግሥትና የሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሀብት ነው፡፡

፪/ መንግሥት የማዕድን ሀብትን በሕዝብ ስም በይዞታው ሥር በማድረግ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን የጋራ ጥቅምና ዕድገት መዋሉን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

፫/ መንግሥት በፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን አማካኝነት የማዕድን ሀብትን ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ ይከለክላል፣ ፈቃዶችን ያስተዳድራል፡፡

## ፮. መሬትን ከልሎ ስለመጠበቅ

፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማናቸ-ውም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ መሬት ለማዕድን ሥራዎች ክፍት ይሆናል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ለሀገሪቱ ጥቅም አስፈላጊ ነው ብሎ ሲያምን የሕዝብ ማስታወቂያ በማውጣት ማናቸውም መሬት የማዕድን ሥራ የማይካሄድበት ነው ብሎ መከልከል ይችላል፡፡

፫/ ማናቸውም ሰው ቀጥሎ በተዘረዘሩት ሥፍራዎች ላይ የማዕድን ምርመራ ፈቃድ፣ ይዞ የመቆየት ፈቃድ ወይም የማምረት ፈቃድ አይሰጠውም፡-

ሀ) ለመቃብርና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች በተከለሉ ሥፍራዎች፤

ለ) የቅድመ ታሪክ ቅሪቶች ባሉባቸው ወይም ብሔራዊ መታሰቢያዎች በቆሙባቸው ሥፍራዎች፤

ሐ) ለመሠረተ ልማት አውታሮች በተከለሉ ቦታዎች፤

መ) ለተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ ወይም ለብሔራዊ ፓርክ በተከለሉ ሥፍራዎች፤

ሠ) ስልጣን የተሰጠው አካል ካልፈ-ቀደ በቀር ከመንደሮች፣ ከከተማዎች ወይም ከውሃ ማጠራቀሚያዎች ወይም ግድቦች በ፭፻ ሜትር ክልል ውስጥ፤ ወይም

ረ) በሌላ ሕግ በተከለከሉ ቦታዎች፡፡

## 5. Custodianship of Mineral Resources

1/ Mineral resources existing in their natural condition on, in, and under the territory of Ethiopia are the property of the government and all the peoples of Ethiopia.

2/ The government shall have the duty to hold mineral resources, on behalf of the peoples, and deploy them for the benefit and development of all Ethiopians.

3/ The government, acting through the Licensing Authority, shall control and administer mineral resources and grant, refuse and manage licenses.

## 6. Reservation of Land

1/ Subject to sub-articles (2) and (3) of this Article, any land in Ethiopia shall be available for mining operations.

2/ Where the Ministry considers it that it is in the best interests of the country, it may, by legal notice, reserve any land from mining operations.

3/ No person shall be granted an exploration license, a retention license or a mining license over an area:

a) reserved for cemeteries and religious sites;

b) containing archaeological remains or national monuments;

c) reserved for physical infrastructure;

d) within areas reserved for natural habitats or national parks;

e) within 500 metres from the boundary of a village, city or water reservoir or dam without the consent of the competent body; or

f) reserved by any other law of the country.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተው የሕዝብ ማስታወቂያ በሥራ ላይ በዋለበት ቀን የማዕድን መብት በጸናበት መሬት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም::

፭/ መንግሥት ለብሔራዊ ጥቅም ሲባል ተገቢው የማካካሻ እርምጃ ተወስዶ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ወይም (፫) መሠረት የተከለለ ማንኛውም ሥፍራ ለማዕድን ሥራ ክፍት እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል::

## ፯. የፈቃድ አስፈላጊነት

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሰረት ተገቢውን ፈቃድ ሳያገኝ የማዕድን ሥራዎች ማካሄድ አይችልም::

፪/ ማንኛውም ሰው የፀና ፈቃድ ሳይኖረው ማንኛውንም ማዕድን በተፈጥሮአዊ ሁኔታው መያዝ፣ ማዘዋወር ወይም መሸጥ አይችልም::

፫/ ሕጋዊ የመሬት ባለይዞታ የሆነ ሰው ሥፍራው በዚህ አዋጅ መሠረት የተያዘ ወይም የተከለከለ ካልሆነ በስተቀር የኮንስትራክሽን ማዕድናትን በይዞታው ሥር ከሚገኝ ሥፍራ ያለክፍያና ፈቃድ ሳያስፈልገው ለንግድ ላልሆነ ዓላማ አምርቶ መጠቀም ይችላል:: ሆኖም የአዋሳኝ ባለይዞታዎችን መሬት ወይም ንብረት አጠቃቀም ማወክ ወይም በእነዚሁ ላይ ጉዳት ማድረስ የለበትም::

፬/ ማንኛውም ሰው ለንግድ ላልሆነ አላማ መንገዶችን፣ ግድቦችን፣ የአውሮፕላን ማረፊያዎችን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችንና ሌሎች የሕዝብ አገልግሎት ሥራዎችን ለመሥራትና ለመጠገን ፈቃድ ሰጪውን ባለሥልጣን አስቀድሞ በማስፈቀድ የኮንስትራክሽን ማዕድናትን ያለክፍያ ማምረትና መጠቀም ይችላል::

፭/ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ፈቃድ ባይኖረውም የአንድን ባለፈቃድ ወይም የሌላ ሰው መብት ሳይነካ የማዕድን ቅኝት ማካሄድ ይችላል::

## ፰. በመንግስት ስለሚካሄዱ የማዕድን ሥራዎች

መንግስት ለጠቅላላ ኢኮኖሚ ዕድገት ወሳኝ ሚና የሚኖራቸውን የማዕድን ሥራዎች በራሱ ወይም ከግል ባለሀብቶች ጋር በቅንጅት ሊያካሂድ ይችላል::

4/ A legal notice issued pursuant to sub-article (2) of this Article, may not affect land which, on the date of the notice is subject to a mineral right.

5/ The government may, where it is in the national interest of the country, authorize the opening of any reserved area under sub-articles (2) or (3) of this Article for mining operations upon providing appropriate compensatory arrangements.

## 7. Requirement of License

1/ No person may undertake mining operations without having obtained the relevant license under this Proclamation.

2/ No person may hold, transport or sell any minerals in their natural state without having a valid license.

3/ A legitimate occupant of land may produce and use for non commercial purpose, free of charge and with out permission of the Licensing Authority, construction minerals from the area he occupies, provided that the area is not excluded or reserved pursuant to the provisions of this Proclamation and provided further that he does not disturb or damage the adjacent occupant's land or property.

4/ Any person may produce and use for non commercial purpose, without charge and with the permission of the Licensing Authority, construction minerals for the construction and maintenance of roads, dams, airports, schools, hospitals and other public works.

5/ Any Ethiopian may conduct reconnaissance without having license provided that he does not interfere with the rights of a licensee or any other person

## 8. Government Mining Operations

The government may undertake mining operations that are vital for the overall economic growth either by itself or in partnership with private investors.

## ፱. የፈቃድ ዓይነቶች

በዚህ አዋጅ መሰረት የሚከተሉት ፈቃዶች ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

፩/ የቅኝት ፈቃድ፤

፪/ የምርመራ ፈቃድ፤

፫/ ይዞ የመቆየት ፈቃድ፤

፬/ ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ፤

፭/ የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ፤ እና

፮/ የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ፡፡

## ፲. ስለምስክር ወረቀት

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት የምስክር ወረቀቶች ሊሰጡ ይችላሉ፡-

፩/ የግኝት ምስክር ወረቀት፤

፪/ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት፡፡

## ፲፩. ፈቃድ ለማግኘት ብቁ ስለመሆን

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ፣ በደንብና በመመሪያ መሠረት ፈቃድ ለማግኘት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችን ካሟላ፣ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ንግድ ማካሄድ የሚችል ከሆነ፣ እንዲሁም የማዕድን ሥራውን ለማከናወን የሚያስፈልገው የገንዘብ አቅም ያለው ወይም ማግኘት የሚችልና የቴክኒክ ችሎታ ያለው ከሆነ ፈቃድ ማግኘት ይችላል፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በባሕላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ላይ ለመሰማራት የገንዘብ፣ የቴክኒክና የሙያ ብቃት አያስፈልገውም፡፡

፫/ የሚከተሉት ፈቃድ ማግኘት አይችሉም፡-

ሀ) ከኪሳራ ያልወጣ ወይም ከአበዳሪዎች ጋር በገባው ሥምምነት መሠረት እዳውን ከሥር ከሥሩ በመክፈል ላይ ያለ ሰው፤

ለ) የማፍረሱ ሂደት የንግድ ማኅበሩን እንደገና ለማቋቋም ወይም ከሌላ ኩባንያ ጋር ለማዋሃድ እስካልሆነ ድረስ በመፍረስ ላይ ያለ የንግድ ማኅበር፤

ሐ) ባሕላዊ የማዕድን ማምረት ሲሆን ኢትዮጵያዊ ዜግነት የሌለው ሰው ወይም አግባብ ባለው የኅብረት ሥራ ማኅበር ሕግ መሠረት ያልተመዘገበ የሰዎች ስብስብ፡፡

## 9. Types of Licenses

The following licenses may be issued under this Proclamation:

1/ a reconnaissance licence;

2/ an exploration licence;

3/ a retention licence;

4/ artisanal mining license;

5/ small scale mining licence; and

6/ large scale mining licence.

## 10. Types of Certificates

The following certificates may be issued under this Proclamation:

1/ a certificate of discovery;

2/ a certificate of professional competence.

## 11. Eligibility for License

1/ A license may be granted to any person who satisfies the requirements of the relevant license set out in this Proclamation, regulations and directives provided that the applicant is qualified to carry on trade under the provisions of the relevant law and possess or has a confirmed access to financial resources and technical competence.

2/ No person is required to possess financial resources, technical and professional competence in order to carry on artisanal mining operation.

3/ No license may be granted or held by:

a) a person who is un-rehabilitated insolvent, or is under a scheme of arrangement with creditors;

b) a business organization which is in liquidation, other than a liquidation which forms a part of a scheme for the reconstruction of the business organization or for its amalgamation with another business organization;

c) a non-citizen of Ethiopia or a group of persons who are not registered as a cooperative society in accordance with the relevant law where it is for artisanal mining license.

፬/ በማጭበርበር ወይም የተሳሳተ መረጃ በማቅረብ ፈቃዱ የተሰረዘበት ባለፈቃድ ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን አንስቶ ለአምስት አመታት ሌላ ፈቃድ ማግኘት አይችልም።

## ፲፪. ስለፈቃድ ማመልከቻ

፩/ አግባብነት ባላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ፈቃድ ለማግኘት፣ ለማሳደስ ወይም ለማስተላለፍ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚቀርብ ማመልከቻ በተወሰነው ፎርም መሰረት የተዘጋጀ ሆኖ፦

ሀ) በዚህ አዋጅ፣ በደንብና በመመሪያ የተገለጹትን ሰነዶች የያዘና ክፍያ የተፈጸመበት፣ እና

ለ) አመልካቹ የንግድ ማኅበር የሆነ እንደሆነ አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሕጋዊ ሰነዶች የያዘ፣

መሆን አለበት።

፪/ ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን የቀረበው ማመልከቻ በቂ መሆኑን ሲያምንበት ወዲያውኑ መዝግቦ ለአመልካቹ ደረሰኝ ይሰጣል።

## ፲፫. ማመልከቻዎች ስለሚስተናገዱበት ቅደም ተከተል

፩/ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የማዕድኑን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ወይም ሌሎች አግባብ ያላቸውን የኢንቨስትመንት ዓላማዎች መሠረት በማድረግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር፦

ሀ) ለከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ፈቃድ የቀረበ ማመልከቻ ለአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድና ለባህላዊ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በቀረቡ ማመልከቻዎች እንዲሁም ለአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ፈቃድ የቀረበ ማመልከቻ ለባህላዊ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በቀረበ ማመልከቻ ላይ ቀዳሚነት ይኖራቸዋል፤

ለ) ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለአንድ ዓይነት ማዕድን በአንድ ቦታ ላይ አንድ አይነት ደረጃ ላላቸው ፈቃዶች ከአንድ በላይ ማመልከቻዎች ከቀረቡለት ማመልከቻዎቹ በቀረቡለት ቅደም ተከተል መሰረት ማስተናገድ አለበት፤

4/ A licensee whose license is revoked due to fraudulent misrepresentation or the presentation of a false statement may not be granted another license for five years starting from the date of revocation of the previous license.

## 12. Applications for License

1/ An application to be submitted to the Licensing Authority for the issuance, renewal or transfer of license in accordance with the relevant provisions of this Proclamation shall be in the form prescribed and:

a) be accompanied by the documentation required by this Proclamation, regulation and directive and with the payment of the prescribed application fee; and

b) in the case where the applicant is a business organization, be accompanied with a documentary proof that it is registered as a business organization in accordance with the relevant law and with other relevant legal documents.

2/ Where the Licensing Authority is satisfied with the application, it shall forthwith register the same and give receipt to the applicant.

## 13. Order of Processing of Applications

1/ Unless the Licensing Authority determines otherwise on the basis of the economic benefit of the minerals or other appropriate investment objectives:

a) an application submitted for a large scale mining license shall take precedence over applications for small scale and artisanal mining lecenses, and an application for small scale mining license shall take precedence over an application for artisanal mining license;

b) if the Licensing Authority receives more than one applications for licenses of the same status covering the same mineral and area, the applications shall be dealt with in the order of receipt;

ሐ) ሁለት ወይም ከዚያ በላይ አመልካቾች ለአንድ ዓይነት ማዕድን በአንድ ቦታ ላይ በአንድ ጊዜ አንድ አይነት ደረጃ ላላቸው ፈቃዶች ማመልከቻዎቻቸውን አቅረበው ከሆነ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ቅድሚያውን ለመወሰን ማመልከቻዎቹን የሚገመግም የቴክኒክ ቡድን ያቋቁማል፤ የቴክኒክ ቡድኑ አመልካቾቹ ያቀረቡትን የቴክኒክ ሥራ እቅድ፣ ለሥራው ሊያወጡ ያሰቡትን የገንዘብ መጠን እና የአመልካቹን ብቃት ገምግሞ በውጤቱ መሠረት ቀዳሚውን ይወሰናል፡፡

፪/ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ አመልካቾች በአንድ ቦታ ላይ የፈቃድ ማመልከቻዎቻቸውን በአንድ ጊዜ ለሚኒስቴሩ እና ለክልል ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን አቅርበው ከሆነ ሚኒስቴሩና የሚመለከተው የክልል ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ማመልከቻዎቹን የሚገመግም የጋራ የቴክኒክ ቡድን ያቋቁማሉ፤ የቴክኒክ ቡድኑ አመልካቾቹ ያቀረቡትን የቴክኒክ ሥራ እቅድ፣ ለሥራው ሊያወጡ ያሰቡትን የገንዘብ መጠንና የአመልካቾቹን ብቃት ገምግሞ በውጤቱ መሰረት ቀዳሚውን ይወስናል፡፡

፫/ ሴት አመልካች ካለችና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት የተካሄደው የግምገማ ውጤት እኩል ከሆነ ቅድሚያ ይኖራታል፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) እና (፫) ድንጋጌዎች ቢኖሩም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻ የቀረበበትን ሥፍራ ጨረታ ሊያወጣበት ይችላል፡፡

## ፲፬. ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ሰዎች ስለማሳወቅ

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ ከመዘገበ በኋላ ጥያቄ የቀረበበትን ቦታ የጂኦግራፊ ኮኦርድኔት በመጥቀስ ሰፊ ተደራሽነት ባላቸው የመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ሦስተኛ ወገኖች እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡

፪/ ፈቃድ እንዳይሰጥ የሚቃወም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት እንዲታወቅ በተደረገ በሰባት ቀናት ውስጥ የቀረበ እንደሆነ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቃውሞውን ለመፍታት እንዲቻል ጉዳዩ በሚመለከታቸው ወገኖች መካከል ድርድር እንዲጀመር ያደርጋል፡፡

፫/ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች የቀረበውን ተቃውሞ በድርድር መፍታት ካልቻሉ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሁለቱንም ወገኖች ክርክር ካዳመጠ በኋላ የቀረበውን ተቃውሞ በመቀበል ወይም ባለመቀበል በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

c) where two or more applicants lodge applications for licenses of the same status at the same time covering the same mineral and area, the Licensing Authority shall constitute a technical team to evaluate the applications and the priority shall be determined on the basis of the evaluation of the technical work plan, the financial proposal, and the technical competency of the applicants;

2/ If two or more applicants submit applications to the Ministry and the licensing authority of a state for licenses covering the same area, the Ministry and the concerned state licensing authority shall appoint a joint technical team to evaluate the applications and the priority shall be determined on the basis of the evaluation of the technical work plan, the financial proposal, and the technical competency of the applicants.

3/ A woman applicant, if any, shall have priority provided that the results of the evaluation conducted pursuant to sub-article (1) or (2) of this Article are equal.

4/ Notwithstanding the provisions of sub-articles (1), (2) and (3) of this Article, the Licensing Authority may, where it deems appropriate, disregard the applications and opt for bidding for the area in question.

## 14. Notification of Interested Parties

1/ The Licensing Authority shall, after registering the application, publicise it to third parties through widely accessible mass media.

2/ If any person objects to the granting of the license within seven days from the date of publicity under sub-article (1) of this Article, the Licensing Authority shall initiate negotiations between the concerned parties to resolve the objection.

3/ If the parties fail to resolve the objection, the Licensing Authority shall hear the presentations of both parties and decide on the upholding or rejection of the objection within 15 working days.

## ፲፭. ስለፈቃዶችና የመሬት ኪራይ መዝገብ

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማዕድን ፈቃዶችና የመሬት ኪራይ መዝገብ ያቋቁማል፣ ይይዛል።

፪/ መዝገቡ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ያመለከቱና የተመዘገቡትን በሙሉ እና ፈቃድ ተሰጥቷቸው ወይም ተከልክለው ከሆነ ይህንኑ ዝርዝር እንዲሁም አግባብ ባላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች፣ በደንብና በመመሪያ የተመለከቱ ዝርዝሮችን ይይዛል።

፫/ ማንኛውም ፈቃድ፣ የመሬት ኪራይ ውል እና ማንኛውም እንዲህ ያለ መብት የተላለፈበት፣ የተዳረገበት፣ የተተወበት፣ የታገደበት፣ የተሰረዘበት፣ በዕዳ የተያዘበት፣ በውርስ የተላለፈበት ወይም በሌላ ሁኔታ የተከናወነበት ሰነድ መመዝገብ አለበት። ከእንዲህ ያለ መብት ጋር የተያያዘ ማንኛውም ሰነድ በተዘጋጀ በ፺ ቀናት ውስጥ ቀርቦ ካልተመዘገበ በሕግ ፊት ዋጋ አይኖረውም።

፬/ መዝገቡን ለመመልከት እንዲቻል ለሕዝብ ክፍት ይሆናል።

፭/ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ዘንድ ለምዝገባ የሚቀርብ ማንኛውም ሰነድ ቅጂ የሚመለከተውን ሥፍራ ለመለየት እንዲቻል ተያይዞ ከሚቀርብ ካርታና ሌላ ፕላን ጋር አግባብ ባለው ሕግ መሠረት መንግሥት በሚይዘው የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች መዝገብ ላይ መመዝገብ አለበት።

## ክፍል ሦስት
## ስለ ፈቃዶች

## ፲፮. የቅኝት ፈቃድ ስለመስጠት

ለቅኝት ፈቃድ የቀረበው የሥራ ፕሮግራም በመሬት ገጽታ ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል የጂኦሎጂ ሥራ የሌለው ከሆነ፣ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የብቻ የሆነ መብት የማያስገኝ ፈቃድ መስጠት አለበት።

## ፲፯. የቅኝት ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ

፩/ የቅኝት ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለጸው ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፣ ሆኖም ይህ ጊዜ ከአስራ ስምንት ወራት በላይ ሊሆን አይችልም።

## 15. Registry of Licenses and Leases

1/ The Licensing Authority shall establish and maintain a registry of licenses and leases.

2/ The registry shall contain details of all registered applications for licenses and all details of their granting or refusal, and any other particulars as may be required by the relevant provisions of this Proclamation, regulation and directive.

3/ Every license, lease and instrument under which mining right is transferred, assigned, surrendered, suspended, revoked, encumbered, inherited or otherwise treated shall be registered in the registry. Each instrument relating to such rights must be presented for registration within 90 days after the date thereof or it shall otherwise be null and void.

4/ The registry shall be open to the public for inspection.

5/ A copy of every instrument required to be filed with the Licensing Authority for registration, together with the map or other plan necessary for identification of the area concerned, shall be filed with the register of immovable property of the government pursuant to the applicable laws.

## PART THREE
## LICENSES

## 16. Granting Reconnaissance License

The Licensing Authority shall grant a non-exclusive reconnaissance license where the work program does not involve any geological work that would result in the disturbance of the surface of the earth.

## 17. Duration of Reconnaissance License

1/ A reconnaissance license shall be valid for the period specified in the license; provided however, that such period shall not exceed 18 months.

፪/ የቅኝት ፈቃድ ሊታደስ አይችልም፡፡

## ፲፰. የምርመራ ፈቃድ ስለመስጠት

፩/ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ የማዕድን ምርመራ ፈቃድ ይሰጣል፡-

ሀ) አመልካቹ የታሰበውን የማዕድን ምርመራ ሥራ በቀረበው የሥራ ፕሮግራም መሰረት ለማከናወን የሚያስችል የገንዘብ አቅምና አስፈላጊው የቴክኒክ ችሎታ ያለው ወይም ለማግኘት የሚችል መሆኑን ካረጋገጠ፤

ለ) የተገመተው የማዕድን ምርመራ ሥራ ወጪ በተወሰነው ዝቅተኛ የምርመራ ወጪ እና በምርመራ ሥራ ፕሮግራሙ መሰረት ከሆነ፤

ሐ) የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማው ተቀባይነት ካገኘ፤ እና

መ) አመልካቹ የቅኝት ፈቃድ የነበረው ከሆነ የዚህኑ ፈቃድ ግዴታዎች ካልጣሰ፡፡

፪/ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የምርመራ ፈቃድ ለአመልካቹ የማይሰጠው ከሆነ ይኸንኑ ውሳኔ በጽሑፍ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል፡፡

## ፲፱. የማዕድን ምርመራ ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና እድሳት

፩/ የማዕድን ምርመራ ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለጸው ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፤ ሆኖም ይህ ጊዜ ከሦስት ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም፡፡

፪/ የምርመራው ፈቃድ እያንዳንዱ ከአንድ ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ ለሁለት ጊዜ ሊታደስ ይችላል፡፡ ባለፈቃዱ ቀደም ሲል ከቀረበው የስራ ፕሮግራም ተጨማሪ የምርመራ ተግባር ማከናወን እንደሚያስፈልግ ካረጋገጠ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በእያንዳንዱ ዓመት የሚታደስ ተጨማሪ ዕድሳት ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ሆኖም ይህ ጊዜ ከአምስት ዓመት ብላይ ሊሆን አይችልም፡፡

፫/ ባለፈቃዱ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎቹን አሟልቶ ከፈፀመ፣ ለዕድሳት የሚጠየቁ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ካሟላ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ፈቃዱን የማሳደስ መብት ይኖረዋል፡፡

2/ A reconnaissance license shall not be renewable.

## 18. Granting Exploration License

1/ The Licensing Authority shall grant an exclusive exploration license where:

a) the applicant has demonstrated that it has acquired or has access to the financial resources and the technical ability to conduct the proposed exploration operation in accordance with the work programme;

b) the estimated exploration expenditure is in accordance with the prescribed minimum exploration expenditure and the exploration work program;

c) the environmental impact plan is approved; and

d) the applicant is not in breach of any obligation of his reconnaissance license, if any.

2/ Where the Licensing Authority refuses to grant an exploration license, it shall notify, in writing, the applicant of the decision and the reasons thereof.

## 19. Duration of Exploration License and Renewal

1/ An exploration license shall be valid for an initial period specified in the license; provided however, that such period shall not exceed three years.

2/ An exploration license may be renewed twice for a period not exceeding one year each. The Licensing Authority may further allow extension of renewal to be made on each year where the licensee proves the necessity to undertake exploration activity beyond the initial work programme. Provided however, that such period shall not exceed five years.

3/ The licensee shall have the right to renew the license provided that he has fulfilled the obligations specified in the license, meets all the requirements in connection with the application for the renewal and is not in breach of any provision of this Proclamation, regulations or directives which constitute grounds for suspension or revocation of the license.

## ፳. ስለማዕድን ምርመራ ባለፈቃድ መብትና ግዴታዎች

፩/ አግባብ ያላቸው የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የማዕድን ምርመራ ባለፈቃድ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል:-

ሀ) ይዞ የመቆየት ፈቃድ እንዲሰጠው የማመልከትና የማግኘት መብት፤

ለ) በማዕድኑና ከምርመራ ፈቃዱ ክልል ጋር በተያያዘ የማምረት ፈቃድ ለማግኘት የማመልከትና ፈቃድ የማግኘት መብት፤

ሐ) በቅድሚያ ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የጽሑፍ ስምምነት በማግኘት ምርመራ፣ ሙከራና ትንተና ለማድረግ አስፈላጊ በሆነው መጠን ማናቸውንም የማዕድን ናሙና ለማውጣትና ለማጓጓዝ፤ ሆኖም ማዕድናቱ የመንግሥት ንብረት ሆነው ይቆያሉ፤ ያለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ፈቃድ አይሸጡም::

፪/ አግባብ ያላቸው የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የማዕድን ምርመራ ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል:-

ሀ) የማዕድን ምርመራ ፈቃዱ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በ፷ ቀናት ውስጥ የምርመራ ሥራውን የመጀመር፤

ለ) የምርመራ ፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች የማክበር፤

ሐ) ምርመራ፣ ሙከራና ትንተና ለማድረግ ያወጣቸውና ያጓጓዛቸው ማዕድናትን ናሙና ቅጂዎች የማስቀመጥ::

## ፳፩. የሥራ ፕሮግራም ስለመለወጥ

፩/ የምርመራ ባለፈቃድ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የሥራ ፕሮግራም በማናቸውም ጊዜ ለመለወጥ ማመልከት ይችላል::

፪/ ማንኛውም የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ የሚቀርብ ማመልከቻ:-

ሀ) ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የሥራ ፕሮግራም ለመተግበር ያላስቻሉትን ሁኔታዎች ማሳየት፣ እና

ለ) የታሰበውን የሥራ ፕሮግራም ማሻሻያ መያዝ፣

አለበት::

## 20. Rights and Obligations of the Holder of an Exploration License

1/ Without prejudice to the appropriat provisions of this Proclamation, the holder of an exploration license shall have the rights to:

a) apply for and be granted a retention license;

b) apply for and be granted a mining license;

c) remove and transport minerals or bulk samples found during the course of exploration in such quantities as may be required to conduct tests or other analysis with the prior written permission of the Licensing Authority; provided however that, such minerals shall remain the property of government and the licensee may not sell them without the prior written approval of the Licensing Authority.

2/ Without prejudice to the appropriat provisions of this Proclamation, the holder of an exploration license shall have the obligations to:

a) commence with exploration activities within 60 days from the date on which the exploration license becomes effective;

b) comply with the terms and conditions of the license;

c) keep duplicates of samples removed and transported for tests or any other analysis.

## 21. Variation of Work Program

1/ The holder of an exploration license may at any time apply to vary the approved work program.

2/ Any application for variation shall:

a) demonstrate the events that prevent the licensee from carrying out the approved work program; and

b) be accompanied with the intended amendments of the work program.

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ የቀረበለትን ጥያቄ ከመረመረ በኋላ፦

ሀ) ተሻሽሎ የቀረበውን የሥራ ፕሮግራም ከተቀበለ ያጸድቀዋል፤ ወይም

ለ) ለውጥ ለማድረግ የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ካደረገው ለውሳኔው ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በመዘርዘር ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳውቀዋል።

፳፪. ከፈቃድ ክልል ላይ የተወሰነውን ስለመልቀቅ

፩/ የምርመራ ፈቃድ እንዲታደስለት የሚጠይቅ ባለፈቃድ በእያንዳንዱ ዕድሳት ወቅት በፈቃዱ ላይ ከተመለከተው የመሬት ክልል ከሩብ እጅ የማያንሰውን ሥፍራ የሚለቅ መሆኑን ማመልከት አለበት።

፪/ የሚለቀቁ ሥፍራዎች ቅርጽ፣ አቀማመጥና ሌሎች ዝርዝር ሁኔታዎች በመመሪያ ይወሰናሉ።

፳፫. ይዞ የመቆየት ፈቃድ ስለመስጠት

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ ለአመልካቹ የብቸኛ መብት የሚሰጥ ይዞ የመቆየት ፈቃድ ይሰጣል፦

ሀ) ባለፈቃዱ በምርመራ ፈቃድ ክልሉ ውስጥ አዋጪ የሆነ የማዕድን ክምችት ማግኘቱን ያስረዳ ሲሆን፣ እና

ለ) የማዕድኑ ክምችት ለጊዜው ባሉት መልካም ያልሆኑ የገበያ ሁኔታዎች ወይም ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ወይም ለጊዜው ማዕድኑን ለማበልጸግ የሚያስችል ቴክኖሎጂ አለመኖር ምክንያት ወዲያውኑ ሊለማ የማይችል ሲሆን።

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በሚከተሉት ሁኔታዎች ይዞ የመቆየት ፈቃድን ሊከለክል ይችላል፦

ሀ) አስፈላጊ የሆነው የማበልጸጊያ ቴክኖሎጂ ያለና የማዕድን ክምችቱ በአትራፊነት ሊመረት የሚችል ሲሆን፣

ለ) መልካም ፉክክርን የሚያግድ ሲሆን፣ ወይም

ሐ) የማዕድን ሀብት በአመልካቹ ቁጥጥር ሥር እንዲሰባሰብ የሚያደርግ ሲሆን።

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ይዞ የመቆየት ፈቃዱን ለአመልካቹ የማይሰጠው ከሆነ ይህንኑ ውሳኔ በጽሑፍ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል።

3/ The Licensing Authority shall, after examining the application for variation:

a) approve the variation if it finds it acceptable; or

b) if it rejects the application, it shall notify, in writing, the applicant the reasons for refusal.

22. **Relinquishment of Portion of License Area**

1/ In applying for each renewal of an exploration license, the licensee shall indicate the portion of the license area, to be relinquished which shall not be less than one fourth of the license area.

2/ The form, orientation and other details regarding relinquishment shall be specified by directive.

23. **Granting Retention License**

1/ The Licensing Authority shall grant an exclusive retention license to the applicant where:

a) the applicant has demonstrated that the discovery of a mineral deposit within the exploration area which is potentially of commercial significance; and

b) the mineral deposit cannot be developed immediately because of adverse market conditions, other economic factors, or unavailable processing technologies, which are of a temporary character.

2/ The Licensing Authority may refuse to grant a retention license if it is established that:

a) the required processing technology is available and the mineral deposit can be mined profitably;

b) it may prevent fair competition; or

c) it may result in the concentration of mineral resources in the hands of the applicant.

3/ Where the Licensing Authority refuse to grant a retention license, it shall notify, in writing, the applicant of the decision and the reasons for refusal.

**፳፬. ይዞ የመቆየት ፈቃድ ዘመንና እድሳት**

፩/ ይዞ የመቆየት ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለጸው ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፤ ሆኖም ይህ ጊዜ ከሶስት ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም።

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች የቀጠሉ መሆናቸውን ባለፈቃዱ ካስረዳ ፈቃዱ ከሦስት አመት ለማይበልጥ ጊዜ አንዴ ይታደሳል።

**፳፭. ይዞ የመቆየት ባለፈቃድ መብትና ግዴታዎች**

፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይዞ የመቆየት ባለፈቃድ የፈቃድ ዘመኑ ከማለቁ በፊት በይዞ መቆየት ፈቃዱ መሠረት የተያዘውን ክልል እና ማዕድን በተመለከተ የማዕድን ማምረት ፈቃድ የማግኘት መብት ይኖረዋል።

፪/ ይዞ የመቆየት ባለፈቃድ:-

ሀ) ያሉትን የገበያና የቴክኒክ ሁኔታዎችና ውጤታቸውን እንዲሁም በተመለከ- ተው ማዕድንና መሬት ላይ ይዞ የመቆየት ፈቃዱ ፀንቶ እንዲቆይ የሚያስፈልግበትን ምክንያት፣ እና

ለ) የፈቃዱ ዘመን ከመጠናቀቁ በፊት የማ ዕድን ማምረት ሥራውን ለመጀመር በማድረግ ላይ ያለውን ጥረት፣

የሚያሳይ ዓመታዊ ሪፖርት ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት።

**፳፮. የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን የማምረት ሥራ ፈቃድ ስለመስጠት**

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ለአመልካቹ ይሰጣል:-

ሀ) የቀረበው የሥራ ዕቅድ ተቀባይነት ካገኘ፤

ለ) አመልካቹ የታሰበውን የማምረት ሥራ በላቀ ደረጃና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል የገንዘብ ምንጭና የቴክኒክ ችሎታ ያለው ወይም ለማግኘት የሚችል መሆኑን ካረጋገጠ፤

ሐ) የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማው ተቀባይ ነት ካገኘ፤ እና

**24. Duration and Renewal of Retention License**

1/ A retention license shall be valid for the period specified in the license, however, that such period shall not exceed three years.

2/ The retention license may be renewed once for a period not exceeding three years where the licensee demonstrates that the conditions specified under sub-article (1) of Article 23 of this Proclamation still prevails.

**25. Rights and Obligations of the Holder of Retention License**

1/ The holder of a retention license shall, subject to sub-article (2) of this Article, have the right to be granted a mining license, in respect of the retention area and mineral in question prior to expiry of the license.

2/ The holder of a retention license shall submit an annual progress report to the Licensing Authority indicating:

a) the prevailing market conditions and technical factors, the effect thereof and the need to hold such retention license over the mineral and land in question; and

b) efforts undertaken by it to ensure that mining operations commence before expiry of the duration of the license.

**26. Granting Large Scale Mining License**

1/ The Licensing Authority shall grant an exclusive large scale mining license to an applicant where:

a) the proposed work program is approved;

b) the applicant has access to financial resources and technical ability to conduct the proposed mining operations optimally and in a safe manner;

c) the environmental impact assessment has been approved; and

መ) አመልካቹ የምርመራ ፈቃድ የነበረው ከሆነ የዚህኑ ግዴታ ያልጣሰ ሆኖ ከተገኘ::

፪/ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማምረት ፈቃድ የማይሰጥ ከሆነ ይህንኑ በጽሑፍ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል::

## ፳፯. የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና ዕድሳት

፩/ የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለጸው ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፤ ሆኖም ይህ ጊዜ ከ፳ ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም::

፪/ የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በእያንዳንዱ እድሳት ወቅት ከ፲ ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ እንዲያገለግል ሊታደስ ይችላል::

፫/ ባለፈቃዱ ክምችቱን ኢኮኖሚያዊ በሆነ ደረጃ ማምረት መቀጠል የሚችል መሆኑን ካሳየ፣ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎ-ቹን አሟልቶ ከፈፀመ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ፈቃዱን የማሳደስ መብት ይኖረዋል::

## ፳፰. የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ስለመስጠት

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉት ሁኔታዎች ከተሟሉ የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ለአመልካቹ ይሰጣል፡-

ሀ) የቀረበው የሥራ ዕቅድ ተቀባይነት ካገኘ፤

ለ) አመልካቹ የታሰበውን የማምረት ሥራ በላቀ ደረጃና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል የገንዘብ ምንጭና የቴክኒክ ችሎታ ያለው ወይም ለማግኘት የሚችል መሆኑን ካረጋገጠ፤

ሐ) የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማው ተቀባይ ነት ካገኘ፤ እና

መ) አመልካቹ የምርመራ ፈቃድ የነበረው ከሆነ የዚህኑ ግዴታ ያልጣሰ ሆኖ ከተገኘ::

፪/ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማምረት ፈቃድ የማይሰጥ ከሆነ ይህንኑ በጽሑፍ ከነምክንያቱ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል::

d) the applicant is not in contravention of any obligations of the exploration license, if any.

2/ If the Licensing Authority refuses to grant a mining license, it shall notify, in writing, the applicant of the decision and the reasons for refusal.

## 27. Duration of Large scale Mining License and Renewal

1/ A large scale mining license shall be valid for the period specified in the license; provided however, that such period shall not exceed 20 years.

2/ A large scale mining license may be renewed for a period not exceeding 10 years each subject to sub-article (3) of this Article.

3/ The licensee shall have the right to renew the license provided that he can demonstrate the continued economic viability of mining the deposit, has fulfilled the obligations specified in the license, and is not in breach of any provision of this Proclamation, regulations or directives which constitute grounds for suspension or revocation of the license.

## 28. Granting Small Scale Mining License

1/ The Licensing Authority shall grant an exclusive small scale mining license to an applicant where:

a) the proposed work program is approved;

b) the applicant has access to financial resources and technical ability to conduct the proposed mining operations optimally and in a safe manner;

c) the environmental impact assessment has been approved; and

d) the applicant is not in contravention of any obligations of the exploration license, if any.

2/ If the Licensing Authority refuses to grant a mining license, it shall notify, in writing, the applicant of the decision and the reasons for refusal.

**፳፱. <u>የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜና ዕድሳት</u>**

፩/ የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለጸው ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፤ ሆኖም ይህ ጊዜ ከ፲ ዓመት በላይ ሊሆን አይችልም።

፪/ የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ፈቃድ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በእያንዳንዱ እድሳት ወቅት ከአምስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ እንዲያገለግል ሊታደስ ይችላል።

፫/ ባለፈቃዱ ክምችቱን ኢኮኖሚያዊ በሆነ ደረጃ ማምረት መቀጠል የሚችል መሆኑን ካሳየ፣ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታ ዎቹን አሟልቶ ከፈፀመ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን በመተላለፍ ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ የሚያበቃ ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ፈቃዱን የማሳደስ መብት ይኖረዋል።

**፴. <u>የአነስተኛና የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች መብትና ግዴታዎች</u>**

፩/ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ያመረታቸውን ማዕድናት ለገበያ የማስተዋወቅና የመሸጥ መብት ይኖረዋል፦

፪/ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ፦

ሀ) ፈቃዱ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በአንድ አመት ውስጥ የምርት ሥራውን መጀመር፣ እና

ለ) የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች ማክበር፣

አለበት።

**፴፩. <u>የሥራ ፕሮግራም ስለመለወጥ</u>**

፩/ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የሥራ ፕሮግራም በማናቸውም ጊዜ ለመለወጥ ማመልከት ይችላል።

፪/ ማንኛውም የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ የሚቀርብ ማመልከቻ፦

ሀ) ተቀባይነት አግኝቶ የነበረውን የሥራ ፕሮግራም ለመተግበር ያላስቻሉትን ሁኔታዎች ማሳየት፣ እና

**29. <u>Duration and Renewal of Small Scale Mining License</u>**

1/ A small scale mining license shall be valid for the period specified in the license; provided however, that such period shall not exceed 10 years.

2/ A small scale mining license may be renewed for a period not exceeding five years each subject to sub-article (3) of this Article.

3/ The licensee shall have the right to renew the license provided that he can demonstrate the continued economic viability of mining the deposit, has fulfilled the obligations specified in the license, and is not in breach of any provision of this Proclamation, regulations or directives which constitute grounds for suspension or revocation of the license.

**30. <u>Rights and Obligations of Holders of Small and Large Scale Mining Licenses</u>**

1/ The holder of a small scale or large scale mining license shall have the rights to market and sell minerals produced.

2/ The holder of a small scale or large scale mining license shall:

a) commence mining operations within one year from the date on which the license becomes effective; and

b) comply with the terms and conditions of the license.

**31. <u>Variation of Work Program</u>**

1/ The holder of a small scale or large scale mining license may at any time apply to vary the approved work program.

2/ Any application for variation shall:

a) demonstrate the events that prevent the licensee from carrying out the approved work program; and

ለ) የታሰበውን የሥራ ፕሮግራም ማሻሻያ መያዝ፤

አለበት::

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሥራ ፕሮግራም ለውጥ ለማድረግ የቀረበለትን ጥያቄ ከመረመረ በኋላ:-

ሀ) ተሻሽሎ የቀረበውን የሥራ ፕሮግራም ከተቀበለ ያጸድቀዋል፤ወይም

ለ) ለውጥ ለማድረግ የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ካደረገው ለውሳኔው ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች በመዘርዘር ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳውቀዋል::

## ፴፪. ስለባህላዊ ማዕድን ማምረት ፈቃድ

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻ ሲቀርብለት አመልካቹ ለፈቃድ ብቁ መሆኑን አረጋግጦ የብቻ የሆነ መብት የሚያስገኝ የባሕላዊ ማዕድን ማምረት ፈቃድ ለአመልካቹ ይሰጣል::

፪/ የባህላዊ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ:-

ሀ) ለባሕላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ በሕግ በተወሰነው የአካባቢ ጥበቃና የጤንነትና የደህንነት ደረጃዎች መሠረት የመስራት ግዴታ አለበት፤

ለ) የፈቃዱን ስምምነቶችና ግዴታዎች ማክበር አለበት::

፫/ የባሕላዊ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተገለጸው ዘመን የፀና ይሆናል፤ ሆኖም ይህ ዘመን ከሦስት አመት አይበልጥም::

፬/ ፈቃዱ ከሦስት ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ ሁለት ጊዜ ሊታደስ ይችላል::

፭/ የክምችቱን ኢኮኖሚያዊ አለኝታ በተሻለ ሁኔታ ለማልማት የላቁ የምርመራና የማምረት ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ሲታመንበት ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የ፺ ቀናት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በቅድሚያ በመስጠት ባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድን ሊሰርዝ ይችላል::

፮/ ባለፈቃዱ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን በሚወስነው አኳኋን በላቀ የምርመራና የማምረት ተግባር ላይ ለመሰማራት የሚያስፈልገው የቴክኒክ ብቃትና የገንዘብ ምንጭ እንዳለው ለማሳየት ከቻለ የቅድሚያ መብት ይሰጠዋል::

b) be accompanied with the intended amendments of the work program.

3/ The Licensing Authority shall, after examining the application for variation:

a) approve the variation if it finds it acceptable; or

b) if it rejects the application, it shall notify, in writing, the applicant the reasons for refusal.

## 32. Artisanal Mining License

1/ The Licensing Authority shall grant an exclusive artisanal mining license where the applicant is eligible for such license.

2/ The holder of an artisanal mining license shall:

a) be obliged to undertake the mining operations in accordance with the environment, health and safety standards prescribed for artisanal mining in the relevant laws;

b) comply with the terms and obligations of the license.

3/ An artisanal mining license shall be valid for the period specified in the license; provided however, that such period shall not exceed three years.

4/ The license may be renewed twice for three years each.

5/ The Licensing Authority may, after giving 90 days prior written notice, revoke an artisanal mining license where it is considered that the deposit requires more advanced exploration and mining method for the best development of its economic potential.

6/ The Licensing Authority shall give preferential treatment to the licensee where the latter shows that he has the necessary technical and financial resources to engage in the advanced exploration and mining as prescribed by the Licensing Authority.

፯/ ባለፈቃዱ የቅድሚያ መብት የማይሰጠው ሲሆን ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን እንደ ባለፈቃዱ ምርጫ አዲስ ማዕድን ማምረቻ ፈቃድ ቦታ ወይም በፈቃዱ መሰረዝ ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት ሊከፈለው የሚገባውን የካሣ መጠን ይወስናል:: ይህም ካሣ ለባለፈቃዱ በተፋጠነ ጊዜ ውስጥ ይከፈለዋል::

## ፴፫. ስለባለፈቃዶች አጠቃላይ መብቶች

፩/ በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተመለከቱት መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ባለፈቃድ እንደ ነገሩ አግባብነት የሚከተሉት አጠቃላይ መብቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) ወደ ፈቃድ ክልል የመግባትና የማዕድን ሥራዎቹን ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ፋብሪካዎችን፣ ማሽነሪዎችንና መሳሪያዎችን የማስገባት፣ ከመሬት በላይ ወይም በመሬት ሥር የሚዘረጉ መሰረተ ልማቶችን የመዘርጋትና የመገንባት፤

ለ) አግባብነት ባላቸው የውሃ ሀብት ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለማዕድን ሥራዎች አስፈላጊ የሆነውን ውሃ በፈቃድ ክልሉ ውስጥ ከሚገኝ ወይም አቋርጦ ከሚያልፍ ከማናቸውም የውሃ ምንጭ የመጠቀም፣ ጥልቅ ወይም ጥልቅ ያልሆነ የውሃ ጉድጓድ የመቆፈር፤

ሐ) በፈቃድ ክልሉ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶችን ለመዘርጋት በፈቃድ ክልሉና በአዋሳኝ ከሚገኝ ቦታ የግንባታ ማዕድናትን የመጠቀም፤

መ) ከፈቃዱ ክልል ውጭ ለሥራው የሚያስፈልገውን ሥፍራ በኪራይ እንዲሰጠው የሚመለከተውን አካል የመጠየቅ፤ ሆኖም የኪራይ ውል ግዴታዎቹ በሚመለከተው አካል የሚወሰኑ ሆኖ የሚጸናበትም ዘመን ከማዕድን ሥራ ፈቃዱ ዘመን የእድሳት ጊዜውን ጨምሮ ማለፍ የለበትም፤

ሠ) የደን ውጤቶችን ስለመቁረጥና በምትካቸው ችግኞችን ስለመትከል የወጡ አግባብ ያላቸው ሕጎችን በማክበር በፈቃድ ክልሉና በተከራየው መሬት ክልል ውስጥ ለማዕድን ሥራው አስፈላጊ የሆኑ የደን ውጤቶችን የመቁረጥና የመጠቀም፤

7/ Where preferential treatment is not accorded to the licensee, the Licensing Authority shall at the option of the licensee grant him another area of mining operation or determine the amount of compensation which shall be paid to the licensee for the loss incurred due to the revocation of the license. Such compensation shall be paid to the licensee promptly.

## 33. General Rights of Licensees

1/ In addition to the rights under other provisions of this Proclamation, a licensee shall, as appropriate, have the rights to:

a) enter the license area and bring to that license area any plant, machinery and equipment, and build and construct any surface or underground infrastructure required for the purposes of his mining operations;

b) use, subject to the relevant water laws, water from any water body, situated on, or flowing through, such land or sink a well or borehole required for mining operations;

c) use construction minerals from within the license area and an area adjacent to the license area as required for erecting essential physical infrastructure within the license area;

d) request the appropriate authority for a lease of land outside of the license area which is required for mining operations; provided however, that the terms and conditions of such lease shall be determined by the appropriate authority and its duration may not in any event exceed the term of the license including any renewal thereof;

e) subject to the applicable laws regarding the cutting of timber and reforestation, cut and use, within the license area and the area of lease, timber which is necessary for mining operations;

ረ) ሌሎች ሰዎች እንዳይገለገሉባቸው መሰናክል የማይፈጥር እስከሆነ ድረስ በነባር የመሠረተ ልማት አውታሮች የመገልገል፤

ሰ) ወደ ፈቃድ ክልሉ ለመድረስ አስፈላጊ የሆነውን መንገድ ለማውጣት የግድ መቆረጥ ያለባቸውን ዛፎች ብቻ የመቁረጥ፤

ሸ) በፈቃዱ መሠረት የገባቸውን ግዴታ ዎች ካሟላ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የፈቃድ ክልሉን በሙሉ ወይም በከፊል ወይም በፈቃዱ ላይ በተጠቀሱት ማዕድናት ላይ ያለውን መብት የመልቀቅ፤

ቀ) ፈቃዱ ሌሎች ማዕድናትን እንዲያካ ትት ወይም የፈቃድ ክልሉ የማዕ ድን ክምችቱን በሙሉ የማያካትት ከሆነ የማዕድን ክምችቱን ሙሉ እንዲሸፍን ተደርጐ እንዲሻሻልለት የመጠየቅ::

፪/ የማጭበርበር ድርጊት ካልተፈፀመ በስተ-ቀር ፈቃድ ለመጠየቅ በቀረበ ማመልከቻ ወይም ፈቃዱ ከመሰጠቱ ወይም የጊዜ ማራዘሚያ ከመደረጉ በፊት በነበረው ሂደት የተፈጸመ የፎርማሊቲ አለመሟላት የባለፈቃዱን መብት አያጓድልበትም::

## ፴፬. ሰለባለፈቃዶች አጠቃላይ ግዴታዎች

፩/ አግባብ ባላቸው የዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች የተመለከቱት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ባለፈቃድ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

ሀ) የማዕድን ሥራውን በጥንቃቄ፣ ትጋ ትና ቅልጥፍና በተሞላበት ሁኔታ ተገቢ በሆኑ ሕጐች፣ ቴክኖሎጂና ለማዕድን ኢንዱስትሪ ተቀባይነት ባገኘ የአሰራር ልምድ መሠረት የማካሄድ፤

ለ) የወኪሎቹን፣ የሠራተኞቹንና የሌ ሎች ሰዎችን ጤንነትና ደህንነት በሚያረጋግጥና በተፈጥሮ አካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳትን ወይም ብክ ላን በተቻለ መጠን መከላከል በሚያ ስችል ሁኔታ የማዕድን ሥራውን የማከናወን፤

ሐ) ለማዕድን ሥራው አስፈላጊ የሆነ ሥልጠናና ትምህርት ሠራተኞቹ እንዲያገኙ የማድረግ፤

መ) በፈቃዱ ክልል፣ በተከራየው መሬትና አዋሳኝ በሆነ መሬት ላይ ሕጋዊ የይዞታ መብት ያላቸውን ሰዎች ላለማወክ ተገቢውን ጥንቃቄ የመውሰድ፤

f) use the existing infrastructure if such use shall not impair the use thereof by other persons;

g) cut such timber as is strictly necessary for access to the license area;

h) relinquish all or part of the license area by giving prior written notice to the Licensing Authority and upon fulfilment of all obligations of the license;

i) modify his license to include other minerals not specified in the license or to include other areas outside his license area where he believes that the license area does not include the entire deposit of minerals.

2/ Except in the case of fraud, no irregularity in the application for or in the proceedings previous to the grant or extension of term of a license shall affect the rights of the licensee.

## 34. General Obligations of Licensees

1/ In addition to the obligations under other relevant provisions of this Proclamation, a licensee shall have the obligations to:

a) carry out mining operations in a prudent, diligent, and efficient manner, in accordance with the appropriate laws, technology and good mining operation practices generally accepted in the mineral industry;

b) conduct mining operations in such a manner as to ensure the health and safety of his agents, employees and other persons, and comply with the applicable laws pertaining to environmental protection;

c) ensure that employees get the training and education necessary for mining operations;

d) take proper precautions not to interfere with other legitimate occupants of the license area, the land covered by a lease and adjacent land;

ሠ) ከሌሎች ባለፈቃዶች ወይም ከሌሎች ሰዎች ጋር በጋራ ለሚጠቀምባቸው በፈቃዱ ክልል ወይም በተከራየው መሬት ላይ ለሚዘረጉ የመሠረተ ልማት አውታሮች ግንባታና ጥገና የመተባበርና ገንዘብ የማዋጣት፤

ረ) በማዕድን ሥራ ላይ እንቅፋት የማይፈጥርበት እስከሆነ ድረስ በነፃ ወይም ለንግድ ዓላማ ሲሆን ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል በዘረጋቸው የመሠረተ ልማት አውታሮች ሌሎች ሰዎች እንዲጠቀሙ የመፍቀድ፤

ሰ) ድንገተኛ ሁኔታ ሲፈጠር ከመሠረተ ልማት አውታሮቹ ላይ ለሚደርሰው ብልሽት ብቻ ካሣ በማስከፈል ሌሎች ሰዎች ወይም መንግሥት በጊዜያዊነት እንዲገለገሉባቸው የመፍቀድ፤

ሸ) ተፈላጊው ችሎታ ላላቸው ኢትዮጵያውያን የቅጥር ቅድሚያ የመስጠት፤

ቀ) በዋጋቸው ተወዳዳሪና በጥራታቸው ተመጣጣኝ ደረጃ ያላቸው እንደልብ ለሚገኙ የሀገር ውስጥ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ቅድሚያ የመስጠት፤

በ) በዚህ አዋጅ፣ በደንብና በመመሪያ መሠረት የሚፈለግበትን ማናቸውንም ክፍያ በወቅቱ የመክፈል፤

ተ) መዛግብቶቹንና ሪኮርዶችን በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ወይም በሕግ ሥልጣን በተሰጣቸው ሌሎች አካላት እንዲመረመሩ የማቅረብ፤

ቸ) የፈቃድ ዘመኑ ሲያበቃ ወይም የፈቃድ ክልሉን ሲለቅ በፈቃድ ክልሉና በተከራየው መሬት ላይ የገነባቸውን ግንባታዎች የማስወገድ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/(ሠ) የተመለከተው የግንባታና የጥገና ወጪ ድልድል በተጠቃሚዎቹ የነፍስ ወከፍ ግልጋሎት መጠን ላይ ተመስርቶ በፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ይወሰናል፡፡

፫/ ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/(ቸ) መሠረት ያላነሳቸውን ግንባታዎች መንግሥት ያለምንም ክፍያ የራሱ ንብረት ሲያደርጋቸው ይችላል፡፡

e) cooperate and contribute financially in the construction and maintenance of infrastructure to be used jointly with other licensees or other persons within the license area or lease area;

f) permit other persons to use his infrastructure freely or, when the use is for commercial purpose, upon the payment of the appropriate fee, provided however, that such use does not impair his mining operations;

g) permit other persons or the government to use temporarily his infrastructure in circumstances of emergency, subject only to the payment of compensation in the event of damage thereto;

h) give preference to the employment of Ethiopian nationals, provided that such persons have the required qualifications;

i) give preference to domestic goods and services, where they are readily available at a competitive price and are of a comparable quality;

j) effect timely all payments required under this Proclamation, regulation and directive;

k) make available all books and records for inspection by the Licensing Authority and other duly authorized officials under the relevant laws;

l) remove constructions in the license area and lease area upon termination of the license or relinquishment of the license area.

2/ The allocation of the cost of construction and maintenance of infrastructure under sub-article (1)(e) of this Article shall be determined by the Licensing Authority on the basis of proportional use of the infrastructure

3/ The government may takeover, free of charge, the constructions not removed by a licensee under sub-article (1)(l) of this Article.

**፴፭. የፈቃድ ክልል ወሰን**

የፈቃድ ክልል፡-

፩/ የማዕድን ማምረት ሥራው በደለል ወይም በጸንስ ተከማችተው የሚገኙ የማዕድን ክምችቶችን የሚመለከት ሲሆን በድንበሮቹ ውስጥ የሚገኘውን መሬትና በድንበሮቹ ዙሪያ ባልተወሰነ ጥልቀት በሚወርድ ቀጥታ መስመር ውስጥ የሚካተተውን የከርሰ ምድር ክልል ይይዛል፤

፪/ የማዕድን ማምረት ሥራው በተራፊ ክምችት ላይ ሲሆን የተራፊ ክምችቱን ብቻ የሚያጠቃልል ይሆናል።

**፴፮. ስለፈቃድ መደራረብ**

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፯(፩) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በአንድ የፈቃድ ክልል ላይ ለተለያዩ ማዕድናት ፈቃዶች ሊሰጥ ይችላል። ሆኖም ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን ተደራራቢው ፈቃድ ቀደም ሲል በተሰጠው ፈቃድ መሠረት በሚካሄዱ የማዕድን ሥራዎች ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ መገምገምና ይህንኑ ለቀድሞው ባለፈቃድ ማሳወቅ አለበት።

**፴፯. ስለፈቃድ ቀዳሚነት**

፩/ ፈቃድ ሰጭው ባለሥልጣን የማዕድኑን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ወይም ሌሎች አግባብ ያላቸውን የኢንቨስትመንት ዓላማዎች መሠረት በማድረግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር፡-

ሀ) የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራዎች በአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ሥራዎች እና በባህላዊ የማዕድን ሥራዎች እንዲሁም የአነስተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራዎች በባህላዊ የማዕድን ማምረት ሥራዎች ላይ ቀዳሚነት ይኖራቸዋል፤

ለ) በአንድ የተወሰነ ክልል ላይ ለተለያዩ ማዕድናት ከአንድ በላይ የሆኑ ተመሳሳይ ደረጃ ያላቸው ፈቃዶች ከተሰጡ በመጀመሪያ የተሰጠ የማዕድን ሥራ ፈቃድ በሌሎች የማዕድን ሥራ ፈቃዶች ላይ ቀዳሚነት ይኖረዋል።

፪/ ፈቃድ በተሰጠበት ክልል ላይ ለተመሳሳይ ማዕድናት በተደራቢ የተሰጠ ፈቃድ ቢኖር በክርክር ላይ ያለው ክልል በቀዳሚው ባለፈቃድ ይዞታ ሥር እንዳለ ሆኖ ይቆጠራል።

**35. Boundaries of License Area**

A license area shall comprise of:

1/ the land within the boundaries and all sub-soil there under to an indefinite depth within the vertical planes passing through each boundary where the mining involves a primary or placer mining operations;

2/ the depth of the deposit compiled where the mining involves mining operations from stockpile or residue.

**36. Superimposition of Licenses**

The Licensing Authority may, subject to Article 37(1) of this Proclamation, grant licenses for different minerals within the same license area subject to notification of the holder of any existing license in the same area upon assessment of the impact of the superimposed license on existing mining operation.

**37. Precedence of Licenses**

1/ Unless the Licensing Authority determines otherwise on the basis of the economic benefit of the minerals or other appropriate investment objectives:

a) a large scale mining operations shall take precedence over small scale and artisanal mining operations, and small scale mining operations shall take precedence over that of artisanal mining operations;

b) if more than one licenses of the same status have been issued covering the same area but for different minerals, the first issued license shall take precedence over mining operations of the other license.

2/ If any area subject to a license is found to be superimposed upon that of another such license for the same minerals, the area in dispute shall be considered to be within the area of the first-issued license.

## ፴፰. ፈቃድ ስለማስተላለፍ

፩/ ከቅኝትና ይዞ ከመቆየት ፈቃዶች በስተቀር ማንኛውም ፈቃድ ፈቃድ ሰጪውን ባለ ሥልጣን በቅድሚያ በማስፈቀድ ሊተላለፍ ይችላል::

፪/ ማንኛውም ፈቃድ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፫) ለተመለከተ ሰው አይተላለፍም።

፫/ ማናቸውም ፈቃድ ሲተላለፍ ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀ መዝገብ ላይ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ካልተመዘገበ በቀር ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም::

## ፴፱. መብትን ስለመተው

፩/ በፈቃዱ ላይ ያገባናል የሚሉ ሰዎች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ ወይም የኪራይ ውል ባለመብት ተቃራኒ ስምምነት ካልኖረው በቀር ቢያንስ የ፲፪ ወራት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በጽሑፍ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በመስጠት የፈቃድ መብቱን ሊተው ይችላል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩ ) መሠረት የፈቃድ ወይም የኪራይ መብቱን የተወ ማንኛውም ሰው ውሉ ጸንቶ ለቆየበት ጊዜ የሚያስከትላቸውን ግዴታዎች ከመፈጸም ነፃ አይሆንም::

## ፵. መረጃዎችን ስለመግለጽ

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ወይም ለሌላ የመንግሥት አካል የቀረበ ማንኛውም መረጃ፣ ሰነድ ወይም ዳታ በባለፈቃዱ ስምምነት ካልሆነ በስተቀር ፈቃዱ ጸንቶ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ በሚስጥር ተጠብቆ መቆየት አለበት።

፪/ መረጃው የሚገለጸው፡-

ሀ) በፍትህ አካላት ለተያዘ ክርክር፣ ማጣራት ወይም ምርመራ ሲሆን፣

ለ) እንደነዚህ ያሉ መረጃዎችን እንዲቀበል በፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ለተፈቀደለት የመንግሥት አማካሪ ወይም ሠራተኛ ሲሆን፣ ወይም

## 38. Transfer of License

1/ Any license, other than a reconnaissance or retention licenses, may be transferred with the prior consent of the Licensing Authority.

2/ No license may be transferred to a person specified under sub-article (3) of Article 11 of this Proclamation.

3/ Any transfer of license shall have no effect unless registered by the Licensing Authority.

## 39. Surrender

1/ The holder of a small-scale or large-scale mining license or a lease may, without prejudice to the rights of persons claiming under the license, surrender any such license or lease by giving to the Licensing Authority, unless otherwise agreed, at least 12 months advance written notice.

2/ Any person who surrenders his license or lease right, pursuant to sub-article(1) of this Article, shall not be released from the liability of performing the duties imposed upon him and due to be performed during the term of the license or lease.

## 40. Disclosure of Information

1/ No information, reports, documents or data submitted to the Licensing Authority or any other government agency under this Proclamation by the licensee shall, for as long as the license remains in effect, be disclosed, except with the consent of the licensee.

2/ Nothing in sub-article (1) of this Article shall operate to prevent the disclosure of information where the disclosure is made:

a) for the purpose of legal proceedings, an inquiry or investigation conducted by an organ of justice administration;

b) to any person being a consultant to the government or officer who is authorized by the Licensing Authority to receive such information;

ሐ) ለጉዳዩ ከሚያስፈልገው በላይ ዝር-ዝር እስካልሆነ ድረስ ለመንግሥት ወይም መንግሥትን በመወከል የማ-ዕድን ሥራዎች ስታቲስቲክስ ለማ-ጠናቀር ሲሆን፣

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለ ከተው ክልከላ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

## ፵፩. ስለሪኮርዶችና ሪፖርቶች

፩/ ማንኛውም ባለፈቃድ የሚከተሉትን መረጃ ዎች የያዙ አግባብነት ያላቸው ሪኮርዶች በሀገር ውስጥ በመያዝ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሪፖርቶች ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) ከጥልቅ ጉድጓድ የወጣ ኮር እና የዚህንም ዝርዝር የተመዘገበ ዳታ ጨምሮ፣ የማዕድን ሥራውንና የተገኙ ውጤቶችን የሚመለከቱ መረጃዎችን፤

ለ) የቅጥር፣ የፋይናንስ፣ የንግድና ሌሎች አግባብ ያላቸው መረጃዎችን::

፪/ ባለፈቃዱ ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በጽሁፍ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖረው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱትን መዝገቦች፣ ከጥልቅ ጉድጓድ የወጣ ኮር ወይም የኮሩን የተመዘገበ ዳታ ማስወገድ ወይም ማጥፋት አይችልም::

## ፵፪. ስለማዕድናት ባለቤትነት፣ ስለሽያጭና ወደ ውጭ ሀገር ስለመላክ

፩/ የምርመራ ፈቃድ ባለይዞታ የሆነ ሰው ማዕድናት ለማውጣት፣ ለማጓጓዝ፣ ለመመርመርና ሚኒስቴሩን አስቀድሞ በማስፈቀድ ናሙናዎችን ወደ ውጭ ሀገር ለፍተሻ ለመላክ ይችላል:: ሆኖም የናሙና ማዕድናት የመንግሥት ንብረት ሆነው ይቆያሉ፤ ያለሚኒስቴሩም ስምምነት ባለፈቃዱ ሊሸጣቸው አይችልም::

፪/ ማዕድን የማምረት ሥራ ባለፈቃድ በፈቃዱ ላይ የተጠቀሱትን ማዕድናት በማውጣት የባለቤትነት መብት ያገኛል::

፫/ ማዕድን የማምረት ሥራ ባለፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከቱትን ማዕድናት በሀገር ውስጥ ለመሸጥ ወይም ወደውጭ ሀገር ለመላክ ይችላል::

## ፵፫. ስለቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነቶች

፩/ ማንኛውም ባለፈቃድ ከማዕድን ሥራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት በሚያደርግበት ጊዜ ስምምነቱን ለሚኒስቴሩ በማቅረብ ማስፈቀድና ማስመ ዝገብ አለበት::

c) for the preparation by or on behalf of the government of statistics in respect of mining operations, provided such disclosure is no more specific in detail than is necessary for the purpose of the statistics concerned.

## 41. Records and Reports

1/ Any licensee shall maintain, in the country, proper records containing the following information and submit reports to the Licensing Authority:

a) information pertaining to his mining operations and the results connected therewith, including borehole core and core-log data;

b) employment, financial, commercial and other relevant information.

2/ The licensee may not dispose of or destroy any record, borehole core or core-log data specified in sub-article (1) of this Article, without the prior written consent of the Licensing Authority.

## 42. Title to, Sale and Export of, Minerals

1/ The holder of an exploration license shall have the right to remove, transport, analyze and, with the prior consent of the Ministry, export samples of minerals for testing; provided however, that such minerals shall remain the property of the government, and the licensee shall not dispose of them without the prior consent of the Ministry.

2/ The holder of a mining license shall obtain title to the minerals specified in the license upon their extraction.

3/ The holder of a mining license shall have the right to sell locally or export the minerals referred to in sub-article (2) of this Article.

## 43. Technology Transfer

1/ Where any licensee concludes a technology transfer agreement in connection with his mining operations, he shall submit the same to the Ministry for approval and registration.

፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት ሲቀርብለት በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፳፩/፲፱፻፹፭ መሠረት አስፈላጊውን ግምገማ አድርጐ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

**፵፬. <u>የማዕድን መብቶችን ስለማገድና ስለመሰረዝ</u>**

፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ እና /፬/ እንደተጠበቁ ሆነው ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የባለፈቃዱ ተግባር በማኅበረሰቡ፣ በአካባቢ ወይም በሠራተኞች ላይ ከባድ አደጋ የሚያስከትል መሆኑን ሲያምንበትና ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ማገድ ብቸኛው መፍትሔ ሆኖ ሲገኝ ፈቃዱን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማገድ ይችላል፡፡ ፈቃድ ሰጪው ባለስ ልጣን እግዱ የሚነሳበትንና ስራ የሚጀምርበትን ቀንም ለባለፈቃዱ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ባለፈቃዱ፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ፣ በደንብ ወይም በመመሪያ የተጣሉበትን ገንዘብ ነክ ግዴታዎቹን ካልፈፀመ፤

ለ) የማዕድን ሥራዎችን በከባድ ቸልተኝነት ወይም ሆን ብሎ አግባብ ባል ሆነ መንገድ ከአካሄደ፤

ሐ) የፈቃዱን መሠረታዊ ስምምነቶች ወይም ግዴታዎች ከጣሰ፤

መ) በ ... መሰረት የማ... የማያካሄድ ከሆነ፤

ሠ) የጸደቀውን የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማና የጤንነትና ደህንነት ደረጃዎችን ጥሶ ከተገኘ፤

ረ) በዚህ በአዋጅ፣ በደንብ ወይም በመመሪያ መሰረት ማቅረብ ከሚገባው ጉዳይ ጋር በተያያዘ ትክክለኛ ያል ሆነ ወይም የተሳሳተ መረጃ አቅርቦ ከተገኘ፤

2/ Where the Ministry receives a technology transfer agreement pursuant to sub-article (1) of this Article, it shall give its decision thereon subsequent to the necessary evaluation in accordance with the Technology Transfer Council of Ministers Regulation No. 121/1993.

**44. <u>Suspension and Revocation of Mineral Rights</u>**

1/ Subject to sub-articles (3) and (4) of this Article, the Licensing Authority may suspend mineral rights partially or fully where it believes that the activity of the Licensee is likely to become an imminent danger to the local community, the environment or its employees provided that such suspension is the only remedy under the prevailing circumstances. The Licensing Authority shall inform the licensee the date by which the suspension lapses and it may resume operation.

2/ Subject to sub-articles (3) and (4) of this Article, the Licensing Authority may revoke any license if the licensee:

a) fails to comply with the financial obligations prescribed in this Proclamation, regulation or directive;

b) conducts mining operations in a grossly negligent or wilfully improper manner;

c) breaches any material term or condition of his license;

d) is not conducting his mining operations in accordance with the work programme;

e) is in breach of the approved environmental impact assessment, and safety and health standards;

f) has submitted false or fraudulent information in connection with any matter required to be submitted under this Proclamation, regulation or directive;

ሰ) የተሟሉ፣ ትክክለኛ የሆኑና ወቅታዊውን ሁኔታ የሚያሳዩ መዝገቦችንና ሪኮርዶችን ካልያዘ፣ ተፈላጊ ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ሰነዶችን በወቅቱ ካላቀረበ ወይም ተፈላጊ ማስታወቂያዎችን በወቅቱ ካልሰጠ፤ ወይም

ሸ) በአግባቡ ሥልጣን የተሰጠው የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሠራተኛ ወደ ፈቃድ ክልሉ ወይም በኪራይ ወደተያዘው ክልል እንዳይገባ ወይም የማዕድን ሥራዎች የሚካሄዱባቸውን ቦታዎች ወይም ተቋማት ወይም የባለፈቃዱን መዝገቦች፣ ሪኮርዶች ወይም ሌሎች ሰነዶች ወይም ማቴሪያሎች እንዳያይ ካደረገ ወይም በሠራተኛው የተሰጠውን ሕጋዊ ትዕዛዝ ወይም መመሪያ ካልፈጸመ፤

ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማንኛውንም ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል።

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) መሠረት እርምጃ ከመውሰዱ በፊት የሚከተሉትን የያዘ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ለባለፈቃዱ ይሰጠዋል፦

ሀ) ፈቃዱን ለማገድ ወይም ለመሰረዝ ምክንያት ናቸው የሚላቸውን ነገሮች፤

ለ) ባለፈቃዱ የፈጸማቸውን መተላለፎች፣ ጥሰቶች ወይም ጉድለቶች ለማረም ሊወስዳቸው የሚገባቸውን እርምጃዎች፤ እና

ሐ) ባለፈቃዱ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሊያይልኝ ይገባል የሚላቸውን ማናቸውም ጉዳዮች በጽሑፍ የሚያቀርብበት ከአምስት የስራ ቀናት ያላነሰ በቂ ቀን።

፬/ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የእገዳ ወይም የስረዛ ማስጠንቀቂያውን የሚያነሳው፦

ሀ) ባለፈቃዱ ለፈቃዱ መታገድ ወይም መሰረዝ ምክንያት ናቸው ተብለው የተዘረዘሩትን ነገሮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫//ለ/ በተሰጠው ማስጠንቀቂያ በተገለጸው ጊዜ ውስጥ በበቂ ሁኔታ ካረመ፣ ካሻሻለ፣ ካስወገደ፣ ወይም እንዳይደገሙ ከተከላከለ፣ ወይም

ለ) እገዳ ወይም ስረዛ ሊፈጽም አይገባም በማለት ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫//ሐ/ መሠረት ያቀረባቸውን ምክንያቶች ከተቀበለ፣

ነው።

g) fails to maintain complete, accurate and current books and records or other documents or materials required or fails to file reports or other documents or fail to give notices required; or

h) fails to grant a duly authorized official of the Licensing Authority access into the license area, the area covered by a lease or to any other site or premises of the mining operations or to his books, records, other documents or materials, or fails to carry out a lawful order or instruction of such official.

3/ Before acting under sub-article (1) or (2) of this Article, the Licensing Authority shall give notice in writing to the licensee:

a) setting out the grounds for considering the suspension or revocation of the license;

b) directing the licensee to take specified measures to remedy any contravention, breach or failure; and

c) specifying a reasonable date of not less than 5 working days, before which the licensee may, in writing, submits any matter for the Licensing Authority to consider,

4/ The Licensing Authority may lift the notice for suspension or revocation of a mineral right where:

a) the licensee complies with the notice contemplated in sub-article (3)(b) of this Article by rectifying, removing, or as appropriate by mitigating the grounds for suspension or revocation, or by preventing the recurrence of such grounds within the time specified in the notice; or

b) where it accepts the reasons supplied by the licensee in accordance with sub-article (3)(c) of this Article for the lifting of the suspension or revocation.

## ክፍል አራት
## ስለምስክር ወረቀቶች

### ፵፭. ለግኝት የምስክር ወረቀት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

፩/ የማዕድን መኖር ወይም ምልክት ያገኘ ማንኛውም ሰው ያለምንም ክፍያ የተወሰነውን ፎርም በመሙላት የግኝት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሊያመለክት ይችላል፡፡

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ የግኝት የምስክር ወረቀት ለማግኘት የቀረበውን ማመልከቻ ተቀብሎ ይመዘግበዋል፡፡

### ፵፮. የግኝት የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

ማዕድናቱ በተገኙበት ቦታ ላይ መኖራቸው ከዚያ በፊት የማይታወቅ ከሆነ፣ ማዕድናቱና የተገኙበት ሥፍራ የብቻ የሆነ ፈቃድ የተሰጠባቸው ወይም ማመልከቻ የቀረበባቸው ወይም የተከለከሉ ካልሆኑ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማመልከቻውን ከተቀበለበት ጊዜ አንስቶ በ፲፭ ቀናት ውስጥ ለአግኚው የግኝት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

### ፵፯. የግኝት የምስክር ወረቀት ዘመንና እድሳት

፩/ የግኝት የምስክር ወረቀት ለአስራ ስምንት ወራት የፀና ይሆናል፡፡

፪/ የግኝት የምስክር ወረቀት አይታደስም፡፡

፫/ የግኝት የምስክር ወረቀት የሚሰጥበት የቦታ መጠን ቢበዛ ከ፲ ካሬ ኪሎ ሜትር አይበልጥም፡፡

### ፵፰. የግኝት የምስክር ወረቀት ባለይዞታ የሆነ ሰው መብትና ግዴታ

፩/ የግኝት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው የምስክር ወረቀቱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማለቁ በፊት አግባብ ላለው የፈቃድ ማመልከቻ የሚጠየቁትን ተፈላጊ ሁኔታ ዎች የሚያሟላ ከሆነ እንደ አግባቡ የምር መራ ፈቃድ ወይም የማምረት ፈቃድ ማመልከቻ የማቅረብ ወይም ፈቃድ ሰጪውን ባለስልጣን በማስፈቀድ ፈቃድ የማግኘት መብቱን ለሌላ ሰው የማስተ ላለፍ መብት ይኖረዋል፡፡

## PART FOUR
## CERTIFICATES

### 45. Application for Certificate of Discovery

1/ Any person who discovers indications or existence of minerals may, free of any charge, apply, in the prescribed form, to the Licensing Authority for a certificate of discovery.

2/ The Licensing Authority shall accept and register the application for a certificate of discovery if the requirements specified in sub-article (1) of this Article are met.

### 46. Issuance of a Certificate of Discovery

The Licensing Authority shall issue a certificate of discovery to the discoverer within fifteen days from the date of registration of the application if the minerals were not previously discovered in the area in question, the minerals and the area in question are not subject to an exclusive license or an application thereof or have not been reserved.

### 47. Duration and Renewal of a Certificate of Discovery

1/ A certificate of discovery shall be valid for 18 months.

2/ A certificate of discovery shall not be renewed.

3/ The maximum area for a certificate of discovery shall not exceed 10 $km^2$

### 48. Rights and Obligations of the Holder of a Certificate of Discovery

1/ The holder of a certificate of discovery shall, prior to the expiry period of the certificate, have the right to apply for an exploration license or a mining license provided that he meets all the requirements pertaining to the relevant application, or transfer his right to another person with the approval of the Licensing Authority.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የግኝት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ባለፈቃድ ከሆነ የቀድሞው ፈቃዱ የተገኙትን ማዕድናት ወይም አዋሳኝ የሆነውን ክልል እንዲጨምር ተደርጐ እንዲሻሻልለት በአማራጭነት የመጠየቅ መብት ይኖረዋል:: ሆኖም የተሻሻለው ክልል ሊፈቀድ ከሚችለው ክልል ጣሪያ ሊያልፍ አይችልም::

**፵፱. <u>የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

፩/ በማዕድን ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ሥራ መሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ተገቢውን የማመልከቻ ክፍያ በመክፈልና የተወሰነውን የማመልከቻ ፎርም በመሙላት ለሚኒስቴሩ ማመልከት ይችላል::

፪/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኝ ማመልከቻውን ተቀብሎ ይመዘግበዋል::

**፶. <u>የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>**

፩/ አመልካቹ የማማከር አገልግሎት ለመስጠት ባመለከተበት ሙያ አስፈላጊው እውቀትና የሥራ ልምድ ያለው መሆኑን ሲያምንበት ሚኒስቴሩ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል::

፪/ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፀንቶ የሚቆይበት ዘመን፣ የሚታደስበትና የሚሰረዝበት ሁኔታ በደንብ ይወሰናል::

**፶፩. <u>የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው መብትና ግዴታ</u>**

፩/ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ማረጋገጫ በተሰጠው ሙያ በማዕድን ዘርፍ ለተሰማራ ማንኛውም ሰው የምክር አገልግሎት መስጠት ይችላል::

፪/ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው ሰው በማማከር ሥራው ላይ ከመሰማራቱ በፊት አግባብ ካለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የንግድ ፈቃድ ማውጣት አለበት::

2/ Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article, where the holder of a discovery certificate is a licensee, he shall, alternately, have the right to be granted an amendment to the license to include the discovered minerals or area adjacent to his existing license, provided that the amended license area does not exceed the maximum allowable area.

**49. <u>Application for Certificate of Professional Competence</u>**

1/ Any Ethiopian who wishes to engage in consultancy services in the mining sector may apply for a certificate of professional competence to the Ministry in the prescribed form and with payment of the prescribed application fee.

2/ The Ministry shall accept and register the application for a certificate of professional competence if the requirements specified in sub-article (1) of this Article are met.

**50. <u>Issuance of a Certificate of Professional Competence</u>**

1/ The Ministry shall issue a certificate of professional competence to the applicant, provided, however, that the applicant has the necessary qualification and experience in the discipline he wishes to consult.

2/ The validity period, renewal and revocation of a certificate of professional competence shall be prescribed by regulation.

**51. <u>Rights and Obligations of the Holder of a Certificate of Professional Competence</u>**

1/ The holder of a certificate of professional competence shall have the right to provide consultancy services to any person engaged in the mining sector in the discipline he is certified for.

2/ The holder of a certificate of professional competence shall be required to obtain the necessary business license from the appropriate government office in order to engage in the consultancy services.

## ክፍል አምስት
## ስለ አስተዳደር

### ፶፪. የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሥልጣንና ተግባር

፩/ የክልል ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን፡-

ሀ) የባሕላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ የመስጠት፤

ለ) ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች፡-

(፩) የኮንስትራክሽንና የኢንዱስትሪ ማዕድናትን በሚመለከት የቅኝት፣ የምርመራና ይዞ የመቆየት ፈቃዶች የመስጠት፤

(፪) የአነስተኛ ደረጃ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ማምረት ፈቃዶች እንዲሁም የአነስተኛና የከፍተኛ ደረጃ ኮንስትራክሽን ማዕድናት ማምረት ፈቃዶች የመስጠት፤ እና

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪//ለ/ ከተመለከተው ውጪ ለሆኑ ማዕድናት የግኝት የምስክር ወረቀት የመስጠት፣

ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ፡-

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩//ሀ/ መሠረት በክልል ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ከሚሰጡት በስተቀር የቅኝት፣ የምርመራ፣ ይዞ የመቆየትና የማዕድን ማምረት ፈቃዶች የመስጠት፤

ለ) ለስትራቴጂካዊ ማዕድናት የግኝት የምስክር ወረቀት የመስጠት፤

ሐ) በማዕድን ዘርፍ የማማከር አገልግሎት ሥራ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የመስጠት፤

መ) ወደውጭ የሚላኩ የማዕድን ናሙናዎችን የመመርመርና የመፍቀድ፤

ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡ ሆኖም የማዕድን ማምረት ፈቃድ የሚሰጠው በቅድሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ይሁንታ በመጠየቅ ይሆናል፡፡

## PART FIVE
## ADMINISTRATION

### 52. Powers and Duties of the Licensing Authority

1/ The licensing authority of a state shall have the powers and duties to:

a) issue artisanal mining license;

b) issue to domestic investors:

(1) reconnaissance, exploration and retention licenses with respect to construction and industrial minerals;

(2) small scale mining licenses for industrial minerals and small and large scale mining licenses for construction minerals;

c) issue certificate of discovery for minerals other than those specified in sub-article (2)(b) of this Article.

2/ The Ministry shall have the powers and duties to:

a) issue reconnaissance, exploration, retention and mining licenses other than those to be issued by a state licensing authority under sub-article (1)(a) of this Article;

b) issue a certificate of discovery for strategic minerals;

c) issue a certificate of professional competence for professionals who wish to engage in consultancy services in the mining sector;

d) conduct testing and give permission for the export of samples of minerals;

provided however, that it shall obtain the approval of the Council of Ministers in respect of issuing any mining license.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ወይም (፪) በተመለከተው መሠረት የተሰጠ ማናቸውም ፈቃድ የባለቤትነት ይዞቱ የተቀየረ እንደሆነ ፈቃዱን የሰጠው ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ከፈቃዱ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ለሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ማስተላለፍ አለበት፡፡

፬/ ማንኛውም ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት ለማዕድን ሥራዎች የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን መቀበል፣ ፕሮሰስ ማድረግ እና ውድቅ ማድረግ ወይም ማጽደቅ፤

ማንኛውም ባለፈቃድ በፈቃዱ የተመለከቱትን ግዴታዎች ለመወጣት አስፈላጊው የገንዘብ ምንጭና የቴክኒክ ብቃት ያለው መሆኑን የማረጋገጥ፤

ሐ) በጨረታ በማወዳደር ወይም ቀጥተኛ በሆነ ድርድር መንግሥትን ወክሎ የማዕድን ስምምነቶችን የማድረግ፤

መ) በዚህ አዋጅ፣ በደንብና በመመሪያ መሠረት ፈቃድ የመስጠት፣ የማደስ፣ የማገድና የመሰረዝ፤

ሠ) የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ ፵፩ የተመለከቱትን መረጃና ሪከርዶች የመቀበል፤

ረ) የማዕድን ሥራዎች በዚህ አዋጅ፣ በደንቦች፣ በመመሪያዎችና አግባብ ባላቸው ስምምነቶች መሠረት መካሄዳቸውን የመቆጣጠርና የማረጋገጥ፤

ሰ) ባለፈቃዱ አስቀድሞ የገባቸው ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው ያመረታቸውን ማዕድናት በሙሉ ወይም በከፊል ሽያጩ በሚከናወንበት ወቅት ባለው የዓለም ገበያ ዋጋ ለመንግሥት፣ ለመንግሥታዊ ድርጅት ወይም ለሌላ ሰው በአገር ውስጥ እንዲሸጥ የማድረግ፤

ሸ) ባሕላዊ ማዕድን ማምረት ሥራ የሚካሄድበትን ሥፍራ እያጠና በሕግ ማስታወቂያ የመከለል፤

ቀ) በዚህ አዋጅ፣ በደንብና መመሪያ መሠረት የሚከፈሉትን ሮያሊቲ፣ የመሬት ኪራይና ሌሎች ክፍያዎች የመሰብሰብና ሂሳቡን የመመርመር፤

3/ When the ownership of any license issued in accordance with the requirements of sub-article (1) or (2) of this Article changes, the Licensing Authority that issued the license shall transfer the documents relating to the license to appropriate Licensing Authority.

4/ Any Licensing Authority shall have the powers and duties to:

a) receive, process and reject or approve any application for mining operations submitted in accordance with this Proclamation;

b) ensure that any licensee has the necessary financial resources and technical competence to fulfill the obligations under the license;

c) enter into mining agreements on behalf of government either by competitive bidding or direct negotiation;

d) issue, renew, suspend and revoke a license in accordance with this Proclamation, regulation and directive;

e) receive, subject to the provisions of Article 40 of this Proclamation, all information and records specified in Article 41 of this Proclamation;

f) inspect and ensure that mining operations are carried out in accordance with this Proclamation, regulations, directives and the applicable agreements;

g) without prejudice to prior commitments of the licensee, require that the licensee sell locally all or a portion of his minerals to government, public enterprise or any other person subject to the payment of the international market price prevailing at the time of the sales transaction;

h) explore and declare by legal notice areas reserved for conducting artisanal mining;

i) collect and audit royalties, rentals, and other fees payable pursuant to this Proclamations, regulation and directive;

በ) ባለፈቃዶች የሚያካሂዷቸው የማዕድን ሥራዎች የአካባቢ ጥበቃን ያገናዘቡና ለማኅበረሰቡ የአካባቢ ልማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ መሆኑን የማረጋገጥ፡፡

**፶፫. <u>የማዕድን ሥራዎች ምክር ቤት</u>**

፩/ ሚኒስቴሩን የሚያማክር የማዕድን ሥራዎች ምክር ቤት ይቋቋማል፡፡

፪/ የማዕድን ሥራዎች ምክር ቤት አባላት ተዋጽኦ፣ ኃላፊነትና ሌሎች ዝርዝር ሁኔታዎች በደንብ ይወሰናሉ፡፡

**፶፬. <u>ስለ ቁጥጥር</u>**

፩/ ማንኛውም ሥልጣን የተሰጠው የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቆጣጣሪ በሥራ ሰዓት ወደማናቸውም የፈቃድ ክልል በመግባት፡-

ሀ) በፈቃድ ክልሉ ላይ ወይም ውስጥ በመካሄድ ላይ ያለን ማናቸውንም እንቅስቃሴ ወይም ሂደት ለመቆጣጠር፤

ለ) ማናቸውንም መዝገብ፣ ሪኮርድ፣ መግለጫ ወይም ሰነድ ለመመርመርና የሰነዱን ወይም የሰነዱን ክፍል ቅጅ ለመውሰድ፤

ሐ) በሥፍራው የሚገኙ ማቴሪያሎችንና መሣሪያዎችን ለመመርመር፤

መ) ማናቸውንም ናሙና ለመውሰድና ለመፈተሽ፣ ለመመርመር፣ ለመተንተንና በአይነት በአይነቱ ለመለየት፤

ሠ) በዚህ አዋጅ፣ በደንብ ወይም በመመሪያ መጣስ ምክንያት ክስ ለመመስረት አስፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎችን፣ ዕቃዎችን፣ መሳሪያዎችን፣ መዝገቦችን፣ መግለጫዎችን ወይም ሰነዶችን ለመያዝና በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ጥበቃ ሥር ለማቆየት፤ እና

ረ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ የተመለከቱትን ተግባራት ለመፈጸም እንዲችል የሚያስፈልጉት ድጋፎች እንዲሰጠው ትእዛዝ ለመስጠት፤

ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/(ሠ) መሠረት ማናቸውም ማቴሪያል፣ መሳሪያ፣ መዝገብ፣ መግለጫ ወይም ሰነድ በፈቃድ ሰጪው ጥበቃ ሥር እንዲቆይ ሲደረግ፡-

j) ensure that mining operations carried out by licensees take into account the environment and are beneficial to the community in the mining areas.

**53. <u>Mining Operations Advisory Council</u>**

1/ A Mining Operations Council shall be established to advise the Ministry.

2/ The composition, responsibilities and other particulars of the Mining Operations Advisory Council shall be determined by regulation.

**54. <u>Inspections</u>**

1/ Any authorized inspector of the Licensing Authority may enter, during office hours, any license area and may:

a) inspect any activity or process carried out in or upon the area in question;

b) inspect any book, record, statement or other document and make copies or extracts thereof;

c) examine any material or appliance found in the area;

d) take samples of any material and test, examine, analyse and classify such samples;

e) seize any material, appliance, book, record, statement or other document which might be relevant to a legal proceeding involving the violation of this Proclamation, regulation or directive and keep it in the custody of the Licensing Authority; and

f) require support necessary for the accomplishment of his inspection in accordance with this sub-article.

2/ Where any material, appliance, book, record, statement or other document is put under the custody of the Licensing Authority in accordance with sub-article (1) (e) of this Article:

ሀ) በይዞታው ወይም በቁጥጥሩ ሥር የነበረ ሰነድ የተያዘበት ሰው ተቆጣጣሪው እየተከታተለው የሰነዱን ወይም የሰነዱን ክፍል ቅጅዎች እንዲወስድ ማድረግ ይቻላል፤

ለ) ከተያዘው ማቴሪያል፣ መሳሪያ፣ መዝገብ፣ መግለጫ ወይም ሰነድ ጋር በተያያዘ ክስ ካልተመሰረተ ወይም በማናቸውም ክርክር ወቅት እንደማስረጃ ሊያገለግል መቻሉ አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም በፍርድ ቤት ትእዛዝ ለተያዘበት ሰው ወዲያውኑ ይመለሳል፡፡

፫/ ተቆጣጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ምርመራውን እንዲያካሄድ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተሰጠውን ደብዳቤ አግባብ ላለው የባለፈቃዱ ሠራተኛ የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

## ፶፭. በሰራተኞች ላይ ጎጂ ተጽዕኖ የሚያስከትሉ እርምጃዎች መውሰድ ስለሚከለከሉባቸው ሁኔታዎች

ማንኛውም ባለፈቃድ ይህን አዋጅ፣ ደንብን፣ መመሪያን ወይም የፈቃድ ግዴታዎቹን አለማክበሩን በሥራ የሚገኝ ሠራተኛ ለፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን በማሳወቁ ምክንያት በሠራተኛው የሥራ ሁኔታ ላይ ጎጂ ተጽዕኖ የሚያደርስ እርምጃ ሊወስድ አይችልም፡፡

## ፶፮. የትርፋማነት ማነስና የማዕድን ማምረት ሥራ መቀነስ

፩/ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲከሰቱ ለፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ያሳውቃል፡-

ሀ) የወቅቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ የማዕድን ሥራው ትርፍ ከገቢው ጋር ያለውን ንጽጽር ለ፲፪ ተከታታይ ወራት በአማካይ ከስድስት በመቶ ያነሰ አድርጎት ከሆነ፣ ወይም

ለ) ማናቸውም የማዕድን ሥራ በማናቸውም የአስራ ሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ከአሥር በመቶ በላይ የሆነ ሠራተኛ ሊያስቀንስ በሚችል ደረጃ የሚቀንስ ወይም የሚቆም ሲሆን፡፡

a) the person from whose possession or control any document is taken shall be allowed, under the supervision of the inspector, to make copies or extracts thereof;

b) if no legal proceedings are instituted in connection with any of the items seized, or if it appears that such item is not required at any trial for the purpose of evidence or upon an order of court, that item shall be returned immediately to the person from whom it was seized.

3/ The inspector shall show his letter of authorization to the appropriate officer of the licensee for conducting inspection under sub-article (1) of this Article.

## 55. Prohibition of Occupational Detriment Against Employees

The holder of any license may not subject any of his employees to any occupational detriment on account of any such employee disclosing information to the Licensing Authority or any authorised person regarding the failure by such holder to comply with any provision of this Proclamation, regulation, directive or his license.

## 56. Reduction of Profitability and Curtailment of Mining Operations

1/ The holder of a small scale or large scale mining license shall notify the Licensing Authority if:

a) the prevailing economic conditions cause the profit to revenue ratio of the relevant mine to be less than six per cent on average for a continuous period of 12 months; or

b) if any mining operation is to be scaled down or to cease with the possible effect that 10 per cent or more of the labour force are likely to be retrenched in any 12 months period.

፪/ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርን ካማከረ በኋላ ጉዳዩ የሚመለከተው የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ የእርምት እርምጃዎች እንዲወስድ በጽሁፍ መመሪያ ሊሰጠው ይችላል፡፡

፫/ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃዱ በተሰጠው መመሪያ መሰረት መፈጸምና የእርምት እርምጃዎቹ መወሰዳቸውን በጽሑፍ ማረጋገጥ አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት
## ስለካሣ ክፍያ

**፶፯. ስለካሣ መርሆዎች**

፩/ የዚህን አዋጅ አላማ ለማስፈጸም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማናቸውንም የማይንቀሳቀስ ንብረት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ለሕጋዊ ባለንብረቱ ተገቢውን ካሣ እንዲከፈል በማድረግ መውረስ ይችላል፡፡ ለዚህም ጉዳይ አፈጻጸም ሲባል የማዕድን ሥራ በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር ፩ሺ፬፻፷ መሠረት የሕዝብ አገልግሎት ሥራ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ባለፈቃድ ከማዕድን ሥራው ጋር በተያያዘ በማናቸውም ንብረት ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡

**፶፰. ስለካሣ ስምምነቶች**

፩/ ማንኛውም ባለፈቃድ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ለባለንብረቱ ስለሚከፈለው ካሣ ከባለንብረቱ ጋር መደራደር አለበት፡፡

፪/ በባለፈቃዱና ባለንብረቱ መካከል በካሣ ስምምነቱ ሁኔታዎችና ግዴታዎች ላይ ስምምነት እንደተደረሰ ባለፈቃዱ ወዲያውኑ የስምምነቱን ቅጅ ለፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን ማቅረብ አለበት፡፡

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የተደረገው የካሣ ስምምነት ቅጂ እንደደረሰው ወዲያውኑ ይመዘግበዋል፡፡

2/ The Licensing Authority may, after consultation with the Ministry of Labour and Social Affairs, direct in writing that the holder of the small scale or large scale mining license in question take appropriate corrective measures.

3/ The holder of the small scale or large scale mining license shall comply with the directive and confirm in writing that the corrective measures have been taken.

## PART SIX
## COMPENSATION

**57. Principles of Compensation**

1/ Where it is necessary for the achievement of the objectives of this Proclamation, the Licensing Authority may expropriate any immoveable property on any land and shall cause the payment of fair compensation by the licensee in accordance with the relevant laws. In this connection, mining operations shall be deemed public purpose within the meaning of Article 1460 of the Civil Code.

2/ Without prejudice to the provisions of sub-article (1) of this Article, any license holder shall be liable for any damage caused to property in connection with its mining operations.

**58. Compensation Agreements**

1/ Any licensee shall negotiate and reach an agreement with respect to the amount of compensation payable to the owner of the property in accordance with the provisions of the relevant laws.

2/ As soon as the terms and conditions have been agreed between the licensee and the property owner, the licensee shall provide a copy of the compensation agreement to the Licensing Authority.

3/ Upon receipt of the copy of the concluded compensation agreement, the Licensing Authority shall forthwith register the same.

**፶፱. ካሣ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ስለሚወሰንበት ሁኔታ**

፩/ ስለሚከፈለው ካሣ ስምምነት ላይ መድረስ ያልቻሉ እንደሆነ ባለፈቃዱ ወይም ባለንብረቱ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እንዲወስንላቸው በጽሁፍ ሊጠይቁ ይችላሉ።

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ካሳውን በመወሰን ሂደት ሁለቱ ወገኖች አለን የሚሉትን ማስረጃና መከራከሪያ እንዲያቀርቡ በማድረግ:-

ሀ) ካሳውን የሚወስንበትን ቀንና ቦታ በመግለጽ ለሁለቱም ወገኖች ያሳውቃል፤

ለ) በቀረበው ማስረጃና መከራከሪያ መሠረት ውሳኔ ይሰጣል፤

ሐ) ውሳኔውን በጽሑፍ ያሰፍራል፤ እና

መ) የውሳኔውን ቅጅ ለሁለቱም ወገኖች ይሰጣል።

## ክፍል ሰባት
## ስለአካባቢ

**፷. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማና የመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ**

፩/ ከቅኝት፣ ከይዞ መቆየት ወይም ከባህላዊ የማዕድን ማምረት ፈቃድ በስተቀር ማንኛውም ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ አመልካች የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማውን አግባብ ላለው መሥሪያ ቤት በማቅረብ ማጸደቅ አለበት።

፪/ ከቅኝት፣ ከይዞ መቆየት ወይም ከባህላዊ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ በስተቀር ማንኛውም ባለፈቃድ ለአካባቢ ተፅዕኖ መልሶ ማቋቋሚያ ወጪ መሸፈኛ የሚውል ፈንድ ይመድባል።

፫/ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድና እንደአግባቡ የማዕድን ምርመራ ባለፈቃድ በፈቃድ ክልሉና በስምምነት በሚወሰን በፈቃድ ክልሉ አካባቢ ለሚኖሩ ነዋሪዎች የማህበረሰብ ልማት እቅድ መሳተፍና ለዚሁ የሚያስፈልግ ወጪ ይመድባል።

፬/ ይህንን አንቀፅ ለማስፈፀም ዝርዝር ጉዳይ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

**59. Determination of Compensation by the Licensing Authority**

1/ Either the licensee or the property owner may, where they are unable to reach an agreement on compensation to be paid, request in writing the Licensing Authority to determine the compensation.

2/ In the process of determining compensation, the Licensing Authority shall allow both parties to present their evidences and arguments after which it shall:

a) fix a place and date for conducting a determination of compensation and notify the parties of the same;

b) make a determination on the basis of the evidences and arguments submitted;

c) record its decision in writing; and

d) give a copy of its decision to each party.

## PART SEVEN
## ENVIRONMENT

**60. Environmental Impact Assessment and Rehabilitation Fund**

1/ Except for reconnaissance license, retention license or artisanal mining license, any applicant for a license shall submit an environmental impact assessment and obtain all the necessary approvals from the competent authority required by the relevant environmental laws of the country.

2/ Except the holder of reconnaissance license, retention license or artisanal mining license, any licensee shall allocate funds to cover the costs of rehabilitation of environmental impact.

3/ To be determined by the licensee area and by agreement, mineral licensee and, as appropriate, exploration licensee shall participate in community development plan of the peoples with in the license area, and shall allocate money for such expenses.

4/ Particulars shall be determined by regulation to be issued for the implementation of this Article.

## ፷፩. <u>ስለማዕድን ሥራ መዘጋት</u>

፩/ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በሚከተሉት ሁኔታዎች የማዕድን መዝጋት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ፈቃድ ሰጪውን ባለሥልጣን ሊጠይቅ ይችላል፡-

ሀ) ፈቃዱ ሲሰረዝ፤

ለ) የማዕድን ሥራው ሲቋረጥ፤

ሐ) የማዕድን ሥራውን ክልል በሙሉ ወይም በከፊል ሲለቅ፤ ወይም

መ) የማዕድኑን ሥራ ሲተው፡፡

፪/ ማመልከቻው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ሁኔታዎች በተከሰቱ በ፩፻፹ ቀን ውስጥ መቅረብ አለበት፡-

፫/ የጤና፣ የደህንነትና የአካባቢ ጥበቃን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች መፍትሔ የተሰጣቸው መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር የማዕድን መዝጋት የምስክር ወረቀት አይሰጥም፡፡

፬/ የማዕድን መዝጋት የምስክር ወረቀት መሰጠቱ፣ ባለፈቃዱን የማዕድኑ ሥራ ከተዘጋ በኋላ በአካባቢው ላይ ሊያደርስ ስለሚችለው ተጽእኖ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማው በሚጠይቀው መሠረት ክትትል የማድረግ ኃላፊነቱን በማናቸውም መንገድ አያስቀረውም፤ ውሉ ጸንቶ ለቆየበት ጊዜ የሚያስከትላቸውን ግዴታዎች ከመፈጸምም ነጻ አያደርገውም፡፡

## ፷፪. <u>የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን መፍትሄ የመስጠት ሥልጣን</u>

፩/ ባለፈቃዱ የሞተ እንደሆነ ወይም ሊገኝ ካልቻለ ወይም ኩባንያ ሲሆን ህልውናው ካከተመ ወይም በኪሣራ ከተዘጋ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተጨማሪ ብክለት እንዳይደርስ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ሥራ ለመስራት የሚያስፈልገው ገንዘብ ባለፈቃዱ ለዚህ ተግባር ብሎ ካኖረው ወይም ለዚህ ጉዳይ የተቀመጠ ገንዘብ ከሌለ ወይም በቂ ካልሆነ ለዚሁ ጉዳይ ከመንግሥት ግምጃ ቤት ከተመደበ ገንዘብ ላይ ወጪ ተደርጎ ይሠራል፡፡

## 61. <u>Mine Closure</u>

1/ The holder of a small scale or large scale mining license shall apply to the Licensing Authority for a mine closure certificate upon:

a) revocation of the license;

b) termination of the mining operations;

c) relinquishment of the whole or any portion of the license area; or

d) abandonment of the mine.

2/ The application shall be made within 180 days from the occurrence of any of the events specified under sub-article (1) of this Article.

3/ No closure certificate shall be issued until the provisions pertaining to health, safety and the environment have been addressed.

4/ The grant of mine closure certificate in no way relieves the licensee from the responsibility to monitor environmental effects after closure of the mine as required in the environmental impact assessment and shall not release the licensee from the liability of performing the duties imposed upon him and due to be performed during the term of the license.

## 62. <u>Remedial Powers of the Licensing Authority</u>

1/ In the event the holder of a license is deceased, cannot be traced, or in the case a company ceases to exist or has been liquidated, the Licensing Authority may take the necessary measures to prevent further pollution or to make the area safe.

2/ The measures contemplated in sub-article (1) of this Article shall be funded from the financial provision established by the holder of the license or, if there is no such provision or it is inadequate, from money appropriated by government treasury for that purpose.

## ክፍል ስምንት
## ስለ ሮያልቲ፣ የገቢ ግብርና ሌሎች ገንዘብ ነክ ጉዳዮች

### ፫. ሮያልቲ

፩/ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ የተመረተውን ማዕድን በንግድ ልውውጥ በሸጠበት ዋጋ ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት ሮያልቲ ይከፍላል።

፪/ በከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች የሚከፈለው ሮያልቲ በሚከተለው መጠን ይሆናል፦

ሀ) ለከበሩ ማዕድናት ፰በመቶ

ለ) በከፊል ለከበሩ ማዕድናት ፮ "

ሐ) ለብረት ነክ ማዕድናት ፭ "

መ) ለኢንዱስትሪ ማዕድናት ፬ "

ሠ) ለኮንስትራክሽን ማዕድናት ፫ "

ረ) ለጨው ፬ "

ሰ) ለጂኦተርማል ፪ "

፫/ በባህላዊና በአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች የሚከፈለው ሮያሊቲ መጠን በክልል ሕጎች ይወሰናል።

### ፬. ለጊዜው ስለሚተመን የሮያልቲ መጠን

፩/ መከፈል የሚገባውን የሮያልቲ መጠን ለመተመን በማይቻልበት ጊዜ ባለፈቃዱ ጊዜያዊ የሮያልቲ ክፍያ ይከፍላል።

፪/ መከፈል ያለበት ሮያልቲ መጠን ሲረጋገጥ ባለፈቃዱ ልዩነቱን ይከፍላል ወይም የከፈለው እላፊ ተመላሽ ይሆንለታል።

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውም ባለፈቃድ የሚጠይቀውን የሮያልቲ ክፍያ ለመቀነስ፣ ለጊዜው ለማንሳት ወይም ለማስቀረት አግባብ ላለው የመንግሥት አካል ሃሳብ በማቅረብ ሊያስወስን ይችላል።

### ፭. የገቢ ግብር

፩/ ማንኛውም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ከማዕድን ሥራ ከሚያገኘው ገቢ በማዕድን ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፶፫/፲፱፻፹፭ (እንደተሻሻለ) መሠረት የገቢ ግብር ይከፍላል።

## PART EIGHT
## ROYALTY, INCOME TAX AND OTHER FINANCIAL REGIME

### 63. Royalty

1/ The holder of a mining license shall pay royalty based on the sales price of the commercial transactions of the minerals produced in accordance with sub-article (2) and (3) of this Article.

2/ The amount of royalty payable by holders of large scale mining licenses shall be at the following rate:

a) precious minerals 8%

b) semi-precious minerals 6%

c) metallic minerals 5%

d) industrial minerals 4%

e) construction minerals 3%

f) salt 4%

g) geothermal 2%

3/ The amount of royalty payable by the holders of artisanal and small scale mining licenses shall be at the rate fixed by the laws of the states.

### 64. Provisional Assessment of Royalty

1/ In the event that it is impractical to assess the amount of any royalty, the licensee shall make a provisional payment of the royalty.

2/ When the amount of the royalty is ascertained, the licensee shall pay any balance or shall be repaid any excess sum paid on such provisional assessment.

3/ The Licensing Authority may, in circumstances it deems appropriate, cause the reduction, suspension or waiver of the payment of royalty by requesting the appropriate government body.

### 65. Income Tax

1/ Any holder of a large scale mining license shall pay income tax in accordance with the Mining Income Tax Proclamation No. 53/1993 (as amended).

፪/ የባህላዊና የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች ከማዕድን ሥራ ከሚያገኙት ገቢ የሚከፍሉት የገቢ ግብር በክልል ሕጎች ይወሰናል።

**፷፮. መረጃ ስለመሰብሰብ**

፩/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ማንኛውም ባለፈቃድ ከሮያሊቲው ክፍያ ጋር በተያያዘ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ማክበሩን ለማረጋገጥ ማናቸውንም የቃል፣ የጽሑፍ ወይም የኤሌክትሮኒክስ መረጃ እንዲያቀርብ ወይም እንዲያሳይ በጽሁፍ ማዘዝ ይችላል።

፪/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚያስፈልጉ መረጃዎች እንዳይቀርቡ ወይም እንዲጠፉ ተደርገዋል ብሎ ሲያምን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፬ መሠረት ምርመራ እንዲካሄድ ሊያዝ ይችላል።

**፷፯. ሮያልቲና የገቢ ግብር ስላለመክፈል**

ባለፈቃዱ መክፈል ባለበት ጊዜ ውስጥ[redacted]፣ የገቢ ግብር ወይም ማናቸውንም ሌላ ክፍያ ሳይከፍል ከቀረ፣ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ያልተከፈሉ ክፍያዎች ተጠናቀው እስኪከፈሉ ወይም ክፍያውን ለመፈጸም የሚያስችል በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ተቀባይነት ያለው ዘዴ እስኪመቻች ድረስ ጉዳዩ ከሚመለከተው ማንኛውም የማዕድን ማምረቻ ቦታ ወይም በባለፈቃዱ ከተያዘ ሌላ የማዕድን ማምረቻ ቦታ ምንም አይነት ማዕድን እንዳይነሳና እንዳይሸጥ በመከልከል ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

**፷፰. የመሬት ኪራይ**

፩/ ማንኛውም ባለፈቃድ በፈቃዱ ላይ ለተመለከተው ክልል የመሬት ኪራይ በየዓመቱ በቅድሚያ ይከፍላል። የኪራዩ መጠን ክልሎች በሚያወጧቸው ሕጎች የሚወሰን ሆኖ ማናቸውም የኪራዩን መጠን የሚለውጥ የሕግ ማሻሻያ ተፈጻሚ የሚሆነው ማሻሻያው ከወጣበት ቀን በኋላ በሚሰጡ ፈቃዶች ላይ ብቻ ይሆናል።

፪/ ማንኛውም ባለፈቃድ ከፈቃድ ክልል ውጭ በኪራይ ለያዘው መሬት በየዓመቱ በቅድሚያ ኪራይ ይከፍላል። የኪራዩ መጠን የኪራዩ መብት በተመሠረተበት ሰነድ የሚወሰን ሆኖ በሰነዱ ውስጥ ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ በስተቀር እስከ ኪራዩ ዘመን መጨረሻ የጸና ይሆናል።

**፷፱. ስለፈቃድ ክፍያ**

በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚሰጡ ፈቃዶችና ፈቃዶቹን ለማሳደስ የፈቃድ ክፍያ ይከፈላል። የክፍያው መጠንና የአከፋፈሉ ሁኔታ እንደአግባቡ በደንብና በክልል ሕጎች ይወሰናል።

2/ Income tax to be paid by holders of artisanal and small scale mining licenses shall be determined by the laws of the states.

**66. Collection of Information**

1/ The Licensing Authority may, by notice in writing, require any licensee to produce or make available any oral, written or [redacted]tronic information as may be required to ensure the proper adherence to the provisions of this Proclamation with [redacted]pect to royalty.

2/ The Licensing Authority may issu[redacted]order for conducting investigation in acc[redacted]ce with Article 54 of this Proclamati[redacted]where it believes that information required under sub-article (1) of this Article is being withheld or destroyed.

**67. Failure to Pay Royalty and Income Tax**

If a licensee fails to pay royalty, incom[redacted] or any other payment on the due da[redacted] the Licensing Authority may by order prohibit the disposal of any mineral from the mining area concerned, or from any other mining area held by the licensee until all outstanding payments have been paid or until an arrangement has been accepted by the Licensing Authority for the payment thereof.

**68. Rentals**

1/ Any licensee shall pay annually in advance surface rentals for the license area. The rate of rentals shall be specified by laws to be issued by states and any amendment thereto shall only apply to licenses issued after the date of amendment.[redacted]

2/ Any licensee shall also pay annually in advance a rental for the area covered by a lease. Such rental shall [redacted] fixed in the instrument granting [redacted]e and shall remain fixed during [redacted], unless the instrument provides otherwise.

**69. License Fees**

License fees shall be paid for the issuance and renewal of licenses in accordance with this Proclamation. The amount and manner of payment of such fees shall be determined by regulation and the laws of states as appropriate.

**በመንግስት ስለሚያዝ አክሲዮን**

መንግሥት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ መሠረት የማዕድን ሥራዎች የማካሄድ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ባለፈቃድ ከሚካሄድ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራዎች ኢንቨስትመንት እስከ አምስት በመቶ የሚደርስ አክሲዮን ያለምንም ክፍያ ሊይዝ ይችላል፡፡ እንዲሁም ስለድርሻው መቶኛ፣ ስለአከፋፈሉ፣ ከተሳትፎ ስለሚመነጩት መብትና ግዴታዎች እና ሌሎች የተሳትፎ ዝርዝር ሁኔታዎች በስምምነት በሚወሰነው መሠረት መንግሥት ተጨማሪ አክሲዮኖችን ሊይዝ ይችላል፡፡

**. ስለዋስትና**

ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ፈቃድ እንዲሰጠው ወይም እንዲታደስለት ወይም ፈቃድ ለማስተላለፍ፣ ለመዳረግ ወይም በዕዳ ለማስያዝ የሚጠይቅ አመልካች ለግዴታዎቹ መፈጸም ማረጋገጫ የሚሆን የገንዘብ፣ የባንክ ወይም ሌላ ዋስትና እንዲያቀርብ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ዋስትና የሚጠየቅበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**. ስለውጭ ምንዛሪ**

፩/ ወደውጭ የሚላኩ ማዕድናት የሚያመርት የከፍተኛ ወይም የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በውጭ ምንዛሪ ካገኘው የሽያጭ ገቢ ውስጥ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ የሚወሰን ድርሻ በመያዝ በውጭ ምንዛሪ ለሚፈጸሙ ክፍያዎች ሊጠቀምበት ይችላል፡፡

፪/ የውጭ ባለሀብት የሆነ የከፍተኛ ወይም የአነስተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ የሚከተሉትን ክፍያዎች ወደ ኢትዮጵያ ባስገባበት የውጭ ምንዛሪ ዓይነት ወይም በሌላ በተፈቀደ የውጭ ምንዛሪ ዝውውሩ በሚፈጸምበት ቀን ባለው የምንዛሪ ተመን መሠረት ከኢትዮጵያ ውጭ ለማዛወር ይችላል፡-

ሀ) ከማዕድን ሥራ ኢንቨስትመንት ካፒታል የተገኘ ትርፍና የትርፍ ድርሻ፣

ለ) ከውጭ አገር በብድር የሚገኝ ዋና ገንዘብና ወለድ፣

ሐ) ከማዕድን ሥራው ጋር ግንኙነት ባለው የቴክኖሎጂ ወይም የሥራ አመራር ስምምነት ምክንያት የሚከፈሉ ገንዘቦች፣ ጥቅሞች ወይም ሌሎች ክፍያዎች፣

መ) የማዕድን ሥራ ድርጅት ፈርሶ ሂሳቡ ሲጣራ የሚገኝ ገቢ፣

**70. Government Participation**

Without prejudice to its right to undertake mining operations under Article 8 of this Proclamation, the government may acquire without cost a participation interest of five percent of any large scale or small scale mining investment. An additional equity participation of the government may also be provided by agreement, which shall specify the percentage, timing, financing, resulting rights and obligation and other details of such participation.

**71. Guarantee**

The Licensing Authority may require the applicant for a license or renewal or for the transfer, assignment or encumbrance of a license to provide cash, bank or other guarantee to secure the applicant's obligations. The conditions of such guarantee shall be determined by directive.

**72. Exchange Control**

1/ A holder of large-scale or small-scale mining license producing exportable minerals may retain a portion of foreign currency earning as may be determined by directives of the National Bank of Ethiopia and use it for settlement of transactions in foreign currencies.

2/ A foreign investor holding a large-scale or small-scale mining license may make the following remittances out of Ethiopia in the currency of investment or in an approved currency at the prevailing rate of exchange on the date of remittance:

a) profits and dividends accruing from mining investment;

b) principal and interest on a foreign loan;

c) fees, royalties or other payments accruing pursuant to technology or management agreement relating to the mining investment;

d) proceeds from the liquidation of a mining business enterprise;

ሠ) አክሲዮን ለሀገር ውስጥ ባለሀብት ሲዛወር ወይም ሲሸጥ ወይም የማዕድን ስራው በከፊል ወይም በሙሉ በሀገር ውስጥ ባለሀብት ባለቤትነት ሥር ሲደረግ የተገኘ ገንዘብ።

፫/ በማዕድን ሥራው ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ የውጭ ሀገር ዜጎች ያገኙትን ደመወዝና ሌሎች ክፍያዎች አግባብ ባለው የውጭ ምንዛሪ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት ወደ ውጭ አገር ለመላክ ይችላሉ።

## ፸፫. ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ስለመሆን

፩/ ማንኛውም የምርመራ ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ለስራው የሚያስፈልጉና በፀደቀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገቧቸው አላቂ ዕቃዎች፣ መሣሪያዎች፣ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ይሆናሉ።

፪/ ማንኛውም የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ወይም የእርሱ ተቋራጭ ለሥራው የሚያስፈልጉና በፀደቀው የስራ ፕሮግራም መሠረት ከውጭ አገር ወደ ኢትዮጵያ የሚያስገባቸው የማምረት ሥራውን ለመጀመር የሚያስችሉ መሣሪያዎች፣ ማሽነሪዎችና ተሽከርካሪዎች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ይሆናሉ።

፫/ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ለንግድ በሆነ መጠን የምርት ሥራውን ለማስጀመር ለመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት ሊያስራው የሚችል ማናቸውንም አላቂ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት ይችላል።

፬/ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ የምርት ሥራውን በላቀ ደረጃ ለማስፋፋት ሲፈልግና የማስፋፊያው እቅድ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሲጸድቅ ለማስፋፊያ ሥራው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችና ማሽነሪዎችን ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ማስገባት ይችላል።

፭/ የባህላዊ፣ የአነስተኛና የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ባለፈቃዶች፣ በፈቃዳቸው መሠረት ያመረቷቸውን ማዕድናት ወደ ውጭ ሲልኩ አስፈላጊው የጉምሩክና የባንክ ፎርማሊቲ ማሟላት እንደተጠበቀ ሆኖ ከማናቸውም የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ይሆናሉ።

፮/ የባህላዊ ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ወይም አሸዋ ወይም ገረጋንቲ ለማምረት የሚያስችል ፈቃድ ያለው ማንኛውም የኮንስትራክሽን ማዕድን ማምረት ባለፈቃድ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፬) የተመለከቱት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ተጠቃሚ አይሆንም።

e) payment from the sale or transfer of shares of a mining investment or acquisition in part or in whole of a mining operation by a domestic investor.

3/ Expatriates employed in mining operations may remit salaries and other payments in accordance with the relevant exchange regulations.

## 73. Exemption from Customs Duties and Taxes

1/ Any consumables, equipment, machinery and vehicles that any holder of an exploration license or his contractor may import into Ethiopia and required for its operations in accordance with the approved work program shall be exempted from customs duties and taxes.

2/ Any equipment, machinery and vehicles that any holder of a small scale or large scale mining license or his contractor may import into Ethiopia and required to start the mining operation in accordance with the approved work program shall be exempted from customs duties and taxes.

3/ The holder of a small scale or large scale mining license may import free of customs duties consumables required to start and sustain commercial production for the first three months.

4/ The holder of a small scale or large scale mining license who wishes to embark on a major mine production expansion shall have the right to import free of customs duties and taxes equipment and machinery needed for the expansion provided that the Licensing Authority has approved the expansion program.

5/ The holder of artisanal mining license, small scale mining license or large scale mining license shall be entitled to export free of customs duties and taxes minerals produced according to the license.

6/ The holder of artisanal mining license or the holder of any construction minerals mining license issued for the mining of sand or selected materials shall not be entitled to exemptions from customs duties and taxes under sub-articles (1) to (4) of this Article.

፯/ ማናቸውም በዚህ አንቀጽ መሠረት ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ የገባ ዕቃ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን በቅድሚያ ሳይፈቅድና ተገቢው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት አይሸጥም:: ሆኖም ዕቃው ተመልሶ ከሀገር የሚወጣ ከሆነ ከጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ነፃ ይሆናል::

## ፸፬. ስለባለፈቃዶች ምዝገባና ስለውክልና

፩/ ማንኛውም ባለፈቃድ አግባብ ባለው ባሥልጣን ዘንድ በንግድ መዝገብ ላይ የመመዝገብና ለፈቃዱ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ ጽሕፈት ቤት የማቋቋም ግዴታ አለበት::

፪/ ባለፈቃዱ በፈቃዱ ላይ የተመለከቱትን ማዕድናት ለማምረት፣ ለመሸጥ ወይም ወደውጭ አገር ለመላክ ወይም ለሥራዎቹ አስፈላጊ የሆኑ ዕቃዎችን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት ወይም የአእምሮ ሥራዎችን በውል ለማግኘት ከሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ፈቃድ አያስፈልገውም::

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ የባለፈቃዱን የጉምሩክና የባንክ ፎርማሊቲዎች የማሟላት ግዴታ አያስቀርም::

## ፸፭. ስለመንግሥት ድጋፍ

፩/ መንግሥት:-

ሀ) የሀገሪቱን ወቅታዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት እገዛ ለሚያደርጉ የማዕድን ሥራዎች፤

ለ) ማዕድናትን በማበልጸግ በሀገር ውስጥ ተጠቃሚነትን ለሚያስፋፉ የማዕድን ሥራዎች፤ እና

ሐ) በኅብረት ሥራ ማኅበራት ለሚከናወኑ ባህላዊ የማዕድን ሥራዎች፤

ማበረታቻና ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል::

፪/ የማበረታቻውና የድጋፉ ዓይነትና ሁኔታ የማዕድን ሥራውን መሠረት ያደረገ ሆኖ በደንብ ይወሰናል::

7/ Any item imported free of customs duties and taxes into Ethiopia pursuant to the provisions of this Article may not be sold in Ethiopia without having obtained permission from the Licensing Authority and paid the required duties and taxes; provided however, that such item may be re-exported free of customs duties and taxes.

## 74. Registration and Representation

1/ Any licensee shall be registered in the registry of trade with the appropriate authority and shall maintain an office in Ethiopia during the entire term of the license.

2/ A licensee shall not be required to obtain any other authorization or permission from any other government office in order to produce, sell or export minerals covered by the license or to import any goods or enter into contract for the acquisition of license of any intellectual property required for mining operations.

3/ The provisions of sub-article (2) of this Article shall not relive a licensee from complying with obligations with customs and bank formalities.

## 75. Government Assistance

1/ The government may provide incentives and assistance to:

a) mining operations that deemed to be vitally important in addressing the immediate socio-economic problems of the country;

b) mining operations that promote the domestic utilizations of the resource produced through processing or beneficiation; and

c) artisanal mining carried out by cooperatives.

2/ The type and mode of incentives and assistance shall depend on the nature of the mining operations and shall be prescribed by regulation.

## ፸፮. ስለመግባባቶችን ስለመፍታት

፩/ የማዕድን ቅኝት፣ ምርመራ፣ ይዞ መቆየት ወይም ማምረትን ከተመለከተ ስምምነት በመነጨ፣ በስምምነቱ አተረጓጐም፣ መጣስ ወይም መቋረጥ ምክንያት ወይም ከእነዚሁ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች በመንግሥትና በባለፈቃድ መካከል የሚፈጠር ማንኛውም ክርክር፣ አለመግባባት ወይም የይገባኛል ጥያቄ በተቻለ መጠን በጋራ ውይይት ይፈታል።

፪/ ጉዳዩ በጋራ ውይይት ሊፈታ ካልቻለ በስምምነቱ ውስጥ በተመለከተው ሥነ ሥርዓት መሠረት በግልግል ዳኝነት ታይቶ ይወሰናል። በግልግል ዳኝነት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና በተዋዋይ ወገኖች ላይ የጸና ይሆናል።

፫/ በግልግል ዳኝነት በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን ቅሬታውን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይግባኝ እንዲታይለት ማቅረብ ይችላል።

## ፸፯. ስለፈቃድ መብት መቋረጥ

፩/ የፈቃድ መብት፡-

ሀ) ባለፈቃዱ የፈቃዱን ክልል በሙሉ ሲለቅ ወይም የፈቃድ መብቱን ሲተው፤

ለ) በዚህ አዋጅ፣ በደንቦችና በመመሪያዎች መሠረት ፈቃዱ በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ሲሰረዝ፤

ሐ) የፈቃዱ ዘመን ከተፈጸመ በኋላ ሳይታደስ ሲቀር፤ ወይም

መ) የወራሾች መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ባለፈቃዱ ሲሞት ወይም ባለፈቃዱ የንግድ ድርጅቱ ከሆነ ሲፈርስ ወይም የመክሰር ውሳኔ ሲሰጥበት፤

ይቋረጣል።

፪/ በስምምነት በሌላ ሁኔታ ካልተገለጸ በቀር የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ ደረጃ የማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ ሲቋረጥ ለማዕድን ሥራዎች ጥቅም ላይ ውለው የእርጅና ቅናሻቸው ሙሉ በሙሉ ያልተፈጸመውን የማይንቀሳቀሱና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች በባለፈቃዱ የሂሣብ መዝገብ ላይ በሚታየው ዋጋቸው መንግሥት ሊወስዳቸው ይችላል። መንግሥት በዚህ መብቱ ካልተጠቀመ ባለፈቃዱ አግባብ ባላቸው ሕጎች መሠረት ንብረቶቹን ለሌላ ሰው ሊያስተላልፍ ይችላል። ይህ የማይሆን ከሆነ ስለ አካባቢው ጥበቃ በገባቸው ግዴታዎች መሠረት እንዲያስወግዳቸው ይገደዳል።

## 76. Settlement of Dispute

1/ Any dispute, controversy or claim between the Licensing Authority and a licensee arising out of, or relating to an agreement for reconnaissance, exploration, retention or mining, or the interpretation, breach or termination thereof shall, to the extent possible, be resolved through negotiation.

2/ In the event that agreement can not be reached through negotiations, the case shall be settled by arbitration in accordance with the procedures specified in the agreement. An arbitral award shall be final and binding upon the parties.

3/ Any party aggrieved by the decision of the arbitration may lodge an appeal to the concerned court.

## 77. Termination of Mining Rights

1/ Mining rights shall terminate if:

a) a licensee relinquishes the whole area or surrenders the license;

b) a license is revoked by the Licensing Authority pursuant to the provisions of this Proclamation, regulations and directives;

c) a license expires without being renewed; or

d) without prejudice to the rights of heirs, a licensee dies, or where the licensee is a juridical person, it is liquidated or declared bankrupt.

2/ Upon termination of mining rights of the holder of a small scale or large scale mining license, the government may, unless an agreement specifies otherwise, acquire all of the immovable and movable property used in the mining operations at a price equal to the then unamortized value of such assets, as shown in the financial book of accounts of the licensee. If the government does not exercise such right, the licensee shall be free to dispose such assets to another person in accordance with the applicable laws, or otherwise he shall be obliged to remove them as required by his environmental obligations.

፫/ የአነስተኛ ወይም የከፍተኛ የማዕድን መብት ሲቋረጥ በፈቃድና በኪራይ ተይዞ በነበረው ቦታ የሚገኙ ጉድጓዶችና ሌሎች ሥራዎች በሰዎች ጤንነት፣ ሕይወትና ንብረት ላይ አደጋ እንዳያስከትሉ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን አጥጋቢ ነው ብሎ በሚቀበለው አኳኋን ባለፈቃዱ እንዲያጥራቸውና መከላከያ እንዲያበጅላቸው ይገደዳል።

## ክፍል ዘጠኝ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፸፰. ቅጣት

ማንኛውም ሰው፦

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፷፯ መሠረት የተሰጠን ትዕዛዝ የጣሰ ወይም ያላከበረ ወይም እንዲህ ያለ ትዕዛዝ መሰጠቱንና በትዕዛዙም መሠረት ማዕድኑን መሸጥ የተከለከለ መሆኑን እያወቀ ማዕድን ከተቀበለ፤

፪/ ይህን አዋጅ፣ ደንብን፣ መመሪያን ወይም የፈቃድ ግዴታዎችን የጣሰ ወይም ያላከበረ፤ ወይም

፫/ በዚህ አዋጅ፣ በደንብ ወይም በመመሪያ መሠረት መቅረብ ካለባቸው ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ትክክል ያልሆነ ወይም የሚያሳስት መረጃ አቅርቦ ከተገኘ፣

እስከ ብር ፪፻ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ አምስት አመት በሚደርስ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /፫/ ድንጋጌ ቢኖርም ስለጥፋት ደረጃና ለእያንዳንዱ ደረጃ የሚገባው ቅጣት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

### ፸፱. ስለቅሬታ አቀራረብ

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት በተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን በየደረጃው ለሚገኙ የፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ኃላፊዎች ማቅረብ ይችላል።

፪/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በተሰጠ አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ይግባኝ እንዲታይለት ለፍርድ ቤት ማቅረብ የሚችለው በፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ያሉ አስተዳደራዊ መፍትሔዎች በሙሉ ተሟጠው ካለቀ በኋላ ነው።

3/ The licensee shall be required on termination of a small scale or large scale mining license, to fence and safeguard to the satisfaction of the Licensing Authority, any pits and such other works in the license or lease area so that the health, life and property of persons may not be endangered.

## PART NINE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 78. Penalty

Any person who:

1/ contravenes or fails to comply with an order given under Article 67 of this Proclamation or, while being aware of such order, receives a mineral the disposal of which is prohibited by the order;

2/ contravenes or fails to comply with any provision of this Proclamation, regulation, directive or the terms and conditions of a license; or

3/ submits inaccurate or misleading information in connection with any matter required to be submitted under this Proclamation, regulation or directive;

shall, be punished with a fine up to Birr 200,000 or an imprisonment up to five years or both.

4/ Notwithstanding the provisions of sub-article (3) of this Article, the degree of offence and the extent of penalty to each offence shall be determined by regulation to be issued for the implementation of this Proclamation.

### 79. Appeal Procedures

1/ Any person who is aggrieved by any administrative decision of the Licensing Authority pursuant to this Proclamation may apply to the officials of the Licensing Authority hierarchically.

2/ No person may apply to the competent court for the review of an administrative decision contemplated in sub-article (1) of this Article until he has exhausted the administrative remedies with the Licensing Authority.

## ፹. ስለአዋጁ አፈጻጸም

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፫/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ለድርድር መነሻ የሚሆን ሞዴል የማዕድን ስምምነት ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡

፬/ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ይህ አዋጅ፣ ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን የመከታተልና የመቆጣጠር ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፹፩. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩/ ይህ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተሰጠ ፈቃድ ወይም የተደረገ የማዕድን ስምምነት ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረነ ድረስ ጸንቶ ለሚቆይበት ቀሪ ዘመን ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡ ከዚያም በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ሊታደስ ይችላል፡፡

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፩/ ድንጋጌ ቢኖርም አንደኛው ወገን አግባብ ባለው ስምምነት ከሚያካሔደው የማዕድን ስራ በሚገኘው ጥቅም ላይ በዚህ አዋጅ ምክንያት ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ጉዳት የደረሰበት ወገን ሲጠይቅ ሁለቱም ወገኖች በቅን ልቦና ተወያይተው አስፈላጊውን ማስተካከያ ለማድረግ ሊስማሙ ይችላሉ፡፡

፫/ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈጠረ ለክስ መነሻ የሚሆን ጉዳይ ወይም የተጀመረ የክርክር ወይም የአፈጻጸም ሂደት ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ጸንተው በነበሩ ሕጎች መሠረት ፍጻሜ ያገኛል፡፡

## ፹፪. የተሻሩና ጸንተው የሚቆዩ ሕጎች

፩/ የማዕድን አዋጅ ቁጥር ፶፪/፲፱፻፹፭ (እንደ ተሻሻለ) በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተሸፈኑትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## 80. Implementation of the Proclamation

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the proper implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry may issue directives necessary for the proper implementation of this Proclamation and regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

3/ The Licensing Authority may prepare model mining agreements to serve as basis for negotiation.

4/ The Licensing Authority shall have the power to follow up and ensure the proper implementation of the provisions of this Proclamation, regulations and directives.

## 81. Transitory Provisions

1/ Any license or mining agreement issued or concluded prior to the coming into force of this Proclamation shall, in so far as it is consistent with this Proclamation, continue in force for the remaining period of its validity, and thereafter, it may be renewed in accordance with the provisions of this Proclamation.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, according to the appropriate agreement where a party undertaking a mineral activity the benefit of which sustains damage due to this Proclamation, up on the request of the other party under damage, both parties may agree to make the necessary correction in good faith mutual discussions.

3/ Any cause of action created or legal proceeding started before the coming into force of this Proclamation shall be dealt with in accordance with the laws in force prior to the effective date of this Proclamation.

## 82. Repeal and Savings

1/ The Mining Proclamation No. 52/1993 (as amended) is hereby repealed.

2/ No law, regulation, directive or practice shall, in so far as they are inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for in this Proclamation.

የማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፹፪/፲፱፻፹፮ ድንጋጌዎች የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እስካልተቃረኑ ድረስ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ እስከሚተኩ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል።

3/ The provisions of the Mining Operations Council of Ministers Regulation No. 182/1994 shall, in so far as they are consistent with this Proclamation, remain in force until replaced by regulation issued pursuant to this Proclamation.

አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

83. **Effective Date**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፰ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም**

**Done at Addis Ababa, this 4th day of August, 2010**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**